
# ጋሻ

ልዩ ዕትም

የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ልሣን | ፖ.ሣ. ቁጥር 1373 አ.አ | ዋጋው 4 ብር ከ35 ሣንቲም | መስከረም 1 ቀን 2018 ዓ.ም | 29ኛ ዓመት ቁጥር 768


እንኳን ለ2018 አዲስ ዓመት በሠላምና በጤና አደረሳችሁ!



## የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስትር ክብርት ኢንጂነር አይሻ መሀመድ የ2018 አዲስ ዓመት መልዕክት

**በቅድሚያ ለጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችን አባላትና አመራሮች፣**

በዓለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ተልዕኮ ላይ ለምትገኙ አባሎቻችን እንዲሁም ለመከላከያ ሚኒስቴር ሲቪል ሰራተኞች እንኳን ለ2018 ዓ.ም አዲስ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ፤ እያልኩ አዲሱ ዓመት የሰላም፣የፍቅርና የድል ዓመት እንዲሆንላችሁ መልካም ምኞቴን እገልፃለሁ፡፡

አዲስ ዓመት በሁላችንም ልብ አዲስ ተስፋና የመታደስ ልዩ ስሜትን የሚፈጥርልን እንደመሆኑ፤ ደበሎፕ ሠራዊታችን ውዷ ሀገራችንን ከየትኛውም ጥቃት ለመጠበቅ የገባውን ቃል ኪዳን ዳግም የሚያድስበት ልዩ አጋጣሚ ነው፡፡

የ2017 ዓ.ም ምንም እንኳን በርካታ ፈተናዎች ያስፍንበት ቢሆንም ጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችን የማይናወጥ ጥንካሬውን፣ ፅናቱንና ቁርጠኝነቱን ያሳየበትና የሀገር ምሰሶ መሆኑን በተግባር ያረጋገጠበትም ነበር፡፡ በመሆኑም በአዲሱም ዓመት ይህንን በማስቀጠል ሁለንተናዊ አቅሙን እየገነባ፣ እየተዋጋና እያመረተ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ሰላም ለማረጋገጥ ደበሎፕ ቃል የሚገባበት እንደሚሆን እተማመናለሁ፡፡

**ውድ የሠራዊታችን አባላትና ሲቪል ሰራተኞች!**

ሀገራችን አሁን ካለችበት ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ለህዝባችን ፅኑ ሰላምን ለማስፈን የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል የገባነውን ቃልኪዳን በማደስ ደበሎፕ ዝግጁነታችንን ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡ ስለሆነም ህዝባዊነትን፣ መልካም ወታደራዊ ዲሲፕሊንንና ግዳጅን በመርህ መሰረት በመፈፀም የድል ባለቤቶች ለመሆን የምንተጋበት አዲስ ዓመት እንዲሆን በቁርጠኝነት መስራት ይጠበቅብናል፡፡

በሌላም በኩል የመከላከያ ሠራዊታችን የሀገር ሃብት ተጠቃሚና ተዋጊ ብቻ ሳይሆን አምራችም እንደመሆኑ ይህንን ገንቢ ሚናውን ለመወጣት በሚያደርገው ጥረት የሲቪል ሰራተኞች ሚና የጎላ ነውና በተቀበልነው አዲሱ ዓመትም ይኸው ተጠናክሮ እንዲቀጥል አደራ ለማለት እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም የመከላከያ ሠራዊታችን ተልዕኮ ኢትዮጵያን ከአደጋ በመጠበቅ ብቻ ሳይሆን ሰላሟን በማፅናት የጀመረችውን የልማትና ዕድገት ጉዞ ማስጠበቅ እንደመሆኑ፤ በዘርፉ የተቀዳጀናቸውን ድሎችና ስኬቶች በማጠናከር ግስጋሴያችንን እንድናፋጥን እያስታወስኩ አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የአንድነትና የስኬት እንዲሆንልን በድጋሚ እመኛለሁ፡፡



## የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ክቡር ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ የ2018 አዲስ ዓመት መልዕክት

የተከበራችሁ በሀገር ውስጥ አኩሪ ግዳጅ በመፈጸም ሰላማችንን በማጽናት ላይ የምትገኙ ጀግናው የመከላከያ ሠራዊት አባላት፣ በዓለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ተልዕኮ በአምባሳደርነት ሚና የኢትዮጵያን መልካምና ገናና ስም እያስቀጠላችሁ ያላችሁ የሠራዊት አባላት፤ እንዲሁም የተቋሙ ሲቪል ሠራተኞች በቅድሚያ እንኳን ለ2018 አዲስ ዓመት በሰላምና በጤና አደረሳችሁ፤ አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የጤናና የድል ዓመት እንዲሆንልን እመኛለሁ!

### ጀግናው የመከላከያ ሠራዊት አባላትና ሲቪል ሠራተኞች፤

የመከላከያ ሠራዊታችን ባለፉት ዓመታት ኢትዮጵያን በሚመጥን ደረጃ በሪፎርም ሁለንተናዊ ብቃቱን እያጠናከረና እያስፋፋ መጥቷል፡፡ ማንኛውንም ግዳጅ በድል በማጠናቀቅ የጠላቶቻችንን አንገት ያስደፋ ስኬት ማረጋገጥ ያስቻለ ዝግጁነትም ገንብቷል፤ ይህንንም በማፈርጠም ላይ ይገኛል፡፡

መከላከያ በወታደራዊ ሳይንስ፣ በወታደራዊ ጥበብና የዕውቀት ክሕሎት እምርታዊ ሽግግር አድርጓል። የአመራርና የተዋጊ የሰው ኃይልን በብዛትና በጥራት በተከታታይ እያፈራ መጥቷል። አዳዲስና ዘርፈ ብዙ አደረጃጀቶችን በመፍጠርና ተቋማትን በመገንባት ጠላቶቻችን ተሳስተው እንዳይተነኩሱን የዲተረንስ አቅማችንን የበለጠ አሳድገናል፡፡ ነባር ወታደራዊ ተቋማትን መልሶ በማልማትና በማዘመን፣ አዳዲስ ተቋማት ባወጣነው የአስር ዓመት ስትራቴጂ ዕቅድ መሰረት በብዛት እየገነባን ነው፡፡ የሠራዊቱን የቤት ዋስትና ለማዳረስ ሠፊ ሥራ እየሰራን ነው፡፡ ወታደራዊ ኢንዱስትሪዎችን በመገንባት ዘመናዊ መሳሪያዎችን ራሳችን አምርተን ለመታጠቅ ብዙ ርቀት ተጉዘናል፡፡ የሠራዊቱን አኗኗር በማሻሻል የግዳጅ አፈጻጸሙ ምቹና ቀልጣፋ እንዲሆን ለማድረግ ተችሏል። ከወዳጅ ሀገሮች ወታደራዊ ተቋማት ጋር መልካም የስራ ግንኙነትና ልምድ ልውውጥ በመፍጠር ወታደራዊ የዕውቀትና ልምድ ሽግግር እንዲዳብር ተደርጓል፡፡ ወታደራዊ ቴክኖሎጂን በመታጠቅ የግዳጅ አፈፃፀም ጥበባችንን ከዘመኑ ጋር ለማዘመን አዳዲስ አቅሞች ፈጥረናል። በአህጉራችን እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰላም ማስከበር ሚናችን እየተጠናከረ የመጣ በመሆኑ ኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ተደማጭነት ያላት አገር እንድትሆን አስችሏል፡፡

### ውድ የመከላከያ ሠራዊት አባላት

በተቋማችን የተከናወኑ ስራዎች በሙሉ የወታደራዊ ዝግጁነት ስራዎች በመሆናቸው የመከላከያ ሠራዊታችንን ሞራልና ሥነ-ልቦና በእጅጉ አሳድገውታል፡፡ ይህም የሠራዊታችንን የአርበኝነትና የቁርጠኝነት ስሜት አሳድጎ ግዳጁን በሚገባ እየተወጣ ጠላቶቻችን የደቀኑትን አደጋም እንዲቀለብስ አስችሎታል፡፡ ሠራዊታችን ጠላቶቻችን ትግል እያሉ አገር ለማፍረስ በጋራና በተናጥል የደቀኑትን አደጋና ፈተና በጀግንነትና በወኔ እየበጣጠሰውም መጥቷል፡፡ ባሳለፍነው 2017 ዓ.ም ጠላቶቻችን ወደ ጣረ ሞት ደረጃ ወርደው በተስፋ መቁረጥ ህዝቡን እየተበቀሉት ነው፡፡ የሚቀጥለው 2018 ዓ.ም ህዝባችን ሙሉ ሰላም ኖሮት አገር እንዲገነባ የቀረውን ተልዕኮ ለመጨረስ አቅደናል፡፡ ኢትዮጵያ ዛሬም ሆነ ነገ በጀግኖች ልጆቿ ታፍራና ተከብራ እንደምትኖር እያረጋገጣችሁ እንደነበር ሁሉ በ2018 ዓ.ም በላቀ ደረጃ እንደምታረጋግጡ መከላከያ ያምናል፡፡ የኢትዮጵያ ዋልታና ማገር የሆነውን ህዝባዊ፣ ዘመናዊና ፕሮፌሽናል ሠራዊት በመገንባት፣ በመምራትና ለድል በማብቃት ላቅ ያለ ኃላፊነት የተወጣችሁ ሁሉ ኮርተንባችኋል፤ መከላከያ ክብርና ምስጋና ያቀርብላችኋል፡፡

ለኢትዮጵያና ለህዝቦቿ ህልውና፣ ለሰላምና ነጻነት በጀግንነት መፋለም አኩሪ ታሪካችሁ ነው፡፡ ስለሆነም ሠራዊታችን ይህን አልደፈር ባይነት፣ ጽናትና ጀግንነት ማስቀጠል ታሪካዊ ክብሩ ነው፡፡

### ጀግናው የመከላከያ ሠራዊት አባላት፤

የውትድርና የሕይወት ዘመን አገልግሎት ስኬት ምንጊዜም በጠንካራ ዝግጁነት፣ ሞራልና ስነልቦና ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የሀገርንና የተቋምን ህልውናና ክብር በጥሞና ተረድቶ የራስን መልካም አሻራ የማሳረፍ ተነሳሽነት ይሻል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ጠላቶቻችን የኢትዮጵያን ሠራዊት በማፈራረስ ኢትዮጵያን አውላላ ሜዳ ላይ ብቻዋን እንዳሻቸው መጫወቻ ለማድረግ ይጎመዣሉ፡፡ የኢትዮጵያን ህልውና እና እጣ ፈንታ በራሳቸው መዳፍ አስገብተው ለመወሰንም ይመኛሉ፡፡ ስለሆነም ሠራዊታችን ይህን ክፉ የጠላቶቻችንን ሴራ በጥሞና በመገንዘብ ኢትዮጵያዊ ሞራልና ሥነ-ልቦናውን በማጥበቅ ጠላቶቻችንንም እንዳይነሱ አድርጎ በኃያል ክንዱ መድፈቅ ይጠበቅበታል፡፡ ስለሆነም በአዲሱ ዓመትም የኢትዮጵያ ህልውና እና ሰላም የሚጸናው በዚህ ኢትዮጵያዊ ሞራልና ወኔ ብቻ መሆኑን አምነን ግዳጃችንን እንደተናንቱ ሁሉ በጽናትና ጀግንነት በማሳካት የሀገራችንና የህዝባችንን ክብር ሙሉ ለሙሉ ማስከበር ይጠበቅብናል፡፡

አዲሱ ዓመት የአዳዲስ ድሎች ዓመት እንዲሆንልን እመኛለሁ!

ወታደርም ሰላምና ጤና ይወዳል፤ይፈልጋል

ስለዚህ ሰላምና ጤና እመኝላችኋለሁ!


የውስጥ ገጾቻችን

ዕቅድን በተግባር ⇨ ገጽ 3

ባህር ኃይላችን በአዲስ ምዕራፍ ⇨ ገጽ 4

የአዲስ ዓመት አስተያየት ⇨ ገጽ 6


«የኢትዮጵያ ሠላም በአዲሱ ዓመት በሠራዊታችን አኩሪ ተጋድሎ አስተማማኝ ይሆናል!»

# ርዕሰ አንቀጽ

## ሠራዊታችን በአዲሱ ዓመት የተሟላ ሰላም ያረጋግጣል!

ስመሳው ኢትዮጵያውያን አዲስ ዓመት ልዩ ነው፡፡ እጅጉን ይናፍቃል፤ በጣም ይጠበቃል። ከፍ ሲልም ይወደዳል፡፡ ድባቡ ሲታወስ መንፈስን ያነቃቃል፡፡ አሮጌውን ዓመት እየሸኘን እንደሆነ አውዱ ይናገራል፡፡ ጋራ ሸንተረሩ፣ ወንዙ ምንጩ ምንጩ፤ ቀየውና ህብር የለበሰው ማሳው መታደስን አንደበት አውጥተው ይመሰክራሉ፡፡ የክረምቱ ፏፏቴ፤ የመስኩ ልምላሜ የአዕዋፍ ዝማሬ መንፈስን ያነቃቃል፡፡ የመታደስ ስሜትን ያጭራል፡፡ አዲስ ዓመት አዲስ ብስራት፤ አዲስ ሕይወት ነው፡፡ በደንብ ያቀራርባል፤ ያፋቅራል፤ እጅግም ልብ ከልብ ያስተሳስራል፡፡ ከክፉ ቀን ያሻግራል፤ የታመመን ያክማል፤ያሽራል፡፡ የተቃቃረን ያስተሳስራል፡፡

አዲስ ዓመት በጋራ ሸንተረሩ ተውቦ ሲነግስ በእጅጉ የሰላም ተስፋ ያነግሳል፡፡ ለፍጡራን ሁሉ ከልብ የተቀዳ የሰላም አየር እንዲነግስ እንመኛለን፡፡ ፍቅር እንዲነግስ ጥላቻና መከፋፋት እስከወዲያኛው እንዲረክስ እንመኛለን፡፡ በአዲስ ዓመት ይህ ምኞት ከልብ የመነጨ ነው፡፡ ከንጹህ ህሊና የተቀዳም ነው፡፡ ስለሆነም አዲስ ዓመት የህዝባችን ትልቁ እሴት የሚገለጥበት የመታደስ አውድ ነው፡፡ ጠንካራ ድልድይም ነው፡፡ ወደ አዲስ ብስራት ደግፎ ያሻግራል፡፡ ያበረታል፤ያጋምዳል፡፡

ስለሆነም በአዲሱ ዓመት አዳዲስ ስኬቶችና ድሎች እንጠብቃለን፡፡ ያለፈውን ዓመት ስኬቶች ለማጥበቅ እንተጋለን፡፡ በአዳዲስ ስኬቶች ውስታውን ልንመልስለት፤ የበለጠ ልናደምቀው፤ የበለጠ ልናከብረው እንጥራለን፡፡ ሀገርን ከፍ በሚያደርጉ ድሎች ልንሞሽረው እንተጋለን፤ እንፋለማለን፤፡፡

የመከላከያ ሠራዊታችንም በአዲስ ዓመት እንዲሁ ነው፡፡ በአዲስ ዓመት የበለጠ አእምሮው ይሰላል፤ ክንዱ ይፈረጥማል፤ ወኔው ይግላል፤ ጽናቱ ይጋረፋል፡፡ በእጅጉ ያብራል። የሀገር ፍቅሩ ይንቀለቀላል፤ ህዝባዊነቱ በልብ ይነግሳል፤ መንፈስን ይቆጣጠራል፤ ድሉ ወገንን ያኮራል፤ ጠላትን ያርዳል፡፡ ስለሆነም ባለፈው ዓመት ያነገሰውን ሰላም ሰንቆ ዘመንን በሀሴት ይሻገራል፡፡

ሠራዊታችን ባለፈው ዓመት በሀገራችን ላይ የተጋረጡ ፈተናዎችን ሁሉ በጀግንነቱ መክቷል፡፡ ሰላማችንን በቀን በጠራራ በትዕቢት ሲቀሙን የዳዱትን ሁሉ በእልህና በወኔ ደቁሷል፡፡ በሚጋረፈው ትንፋሹ፤ ብረት በሚያቀልጠው ክንዱ ሳይመለሱ ደቁሷቸዋል፡፡ ከአፈር ደባልቋቸዋል፡፡ የኢትዮጵያን ሰላም የመቀማት የክፋት ህልማቸውን፤ ክብሯን የማውረድ ቅዠታቸውን ቀዳዶታል፡፡ እንደ ጉም አብንኖታል፡፡ ስለሆነም በጠላቶቻችን መቃብር ላይ ከአጽናፍ አጽናፍ የናኘ የሰላም ሰንደቅ አውለብልቧል፡፡ የኢትዮጵያን ክብር ከፍ ከፍ አድርጓል። የህዝቧን ነጻነት አንግሷል፡፡ የራሱንም አልደፈር ባይነት በድሉ አረጋግጧል፡፡ እንደ አለት የደደረ ወታደራዊ አቅሙን አሳይቷል፡፡

እንዲሁም የሥነ-ልቦና ምጥቀቱን፤ የሞራል ልዕልናውን በጀግንነቱና በጽናቱ አረጋግጧል። ለሀገር ክብር ቀናኢነቱን፤ ለህዝብ ነጻነትና ደህንነት በክብር ሟችነቱን በላብና በደሙ በደማቁ ጽፏል፡፡ ዳር ድንበራችንን በአጽሙ ፍላጻ አጥብቆ ማግሯል፡፡ ሠራዊታችን በድሉ ኢትዮጵያ በአበው ቃል ኪዳን የታሰረች፤ በተወራራሽ ጀግንነት የጸናች፤ በትውልዶች የተገነባች፤ በፈተና እንደ ወርቅ የነጠረች፤ በጠላቶቿ ሴራ የበለጠ በአትንኩኝ ባይነት የፈረጠመች ሀገር እንደሆነች አስመስክሯል፡፡

ስለሆነም በአዲሱ ዓመትም ሠራዊታችን ይህን ድል ነው የሚያስቀጥለው፡፡ የበለጠ ያደምቀዋል፡፡ የበለጠ ያፈረጥመዋል፡፡ ወታደራዊ ፕሮፌሽናሊዝምን በመላበስ የኢትዮጵያ ጋሻና መከታ ሆኖ ይቀጥላል፡፡ አዳዲስ ወታደራዊ ተቋማቱን እያለማ ክንዱን ያበረታል፡፡ አዕምሮውን ያሰላል፡፡ ዲስፕሊኑን ያጠብቃል፤ ህዝባዊነቱን ያስተሳስራል፡፡

ሠራዊታችን የሀገር ዋልታና ማገር ፡፡ ኢትዮጵያ ብዙ አልማለች፡፡ ብዙ ሰንቃለች። ይህ ህልም እውን የሚሆነው በሰላም ነው፡፡ የሀገር ሉዓላዊነት የህዝብ ነጻነትና ክብር በዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ላይ ነው የሚጸኑት፡፡ ሠራዊታችን የዚህ ሰላም ዋስትና ነው፡፡ ስለሆነም በአዲሱ ዓመትም ሰራዊታችን የሰላም አምባሳደር ነው፡፡ ወታደራዊ ቁመናውን እያጎለበተ ከህዝባችን ጋር እጅና ጓንት ሆኖ ሰላማችንን ያጸናል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃም የሰላም አምባሳደርነቱን ያስመሰክራል፡፡ ተመራጭ የሰላም ኃይል መሆኑን በስኬቱ ያረጋግጣል፡፡

የመከላከያ ሠራዊታችን ካለፈው ዓመት በተሻለ በአዲሱ ዓመትም አዳዲስ ድሎች ይቀዳጃል፡፡ ይህ ድል ጠንካራ ተቋምና ጠንካራ ሠራዊት በመፍጠር ነው የሚሳካው፡፡ ወታደራዊ ፕሮፌሽናሊዝም ዓለም አቀፍ ስታንዳርድ ነው፡፡ በዚህ ልክ ራስን ማብቃት፣ ማደራጀትና ማስታጠቅ ይጠይቃል፡፡ የፈጠራና ምርምር ዕውቀትና ክህሎት መካን ይገባል። የሠራዊቱን ግዳጅና ኑሮ ምቹ፣ ቀልጣፋና ዘመናዊ የሚያደርጉ አሰራሮችን መተግበር ያስፈልጋል፡፡ በመልካም ስኬቶች የውትድርና አገልግሎት ክብርን ከፍ ማድረግ ይገባል። እንዳለፈው ዓመት ሁሉ የህዝባችንን፤ የወጣቶችንና የወዳጅ ሀገሮችን ልብ የሚማርኩ ተቋማት መገንባታችንን መቀጠል አለብን፡፡ ኢትዮጵያ የፓን አፍሪካ የነጻነት ትግል አብሪ የነጻነት ሰንደቅ መሪ እንደሆነችው ሁሉ በወታደራዊ ፕሮፌሽናሊዝምም ልቃ እንድትገኝ መስራት ይኖርብናል፡፡ ይህም እየተሳካ ነው።

ስለሆነም እነዚህ አቅሞች የሰላም አቅሞች ናቸው፡፡ ሠራዊታችን በአዲሱ ዓመትም የተሟላ ሰላም እንዲያረጋግጥ መሰረቶች ናቸው፡፡ አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የጤናና የድል ዓመት እንዲሆንልን እንመኛለን፡፡

በኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስቴር
የመከላከያ ሠራዊት ሥነ-ልቦና ግንባታ ዋና ዳይሬክቶሬት
በየሁለት ሣምንቱ የሚታተም
ህዳር 1988 ዓ.ም ተመሠረተ
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
ስልክ ቁጥር - 011-1248629
011-1249694
ፋክስ - 011-1249552
ጋሻ ጋዜጣ ቡድን መሪ (ዋና አዘጋጅ) ኮሎኔል መሀመድ ሙሳ
ጋዜጣ ስርጭት መኮንን - ሻለቃ እብዩ ብርሃኑ
ትምህርትና መዝናኛ ዝግጅት ዴስክ አስተባባሪ - ሻለቃ ሰለሞን ሁነኛው
ዜናና ወቅታዊ ዝግጅት ዴስክ አስተባባሪ - መ/አ አባቱ ወ/ማርያም
ግራፊክስ ዲዛይን - መ/አ አፀደ ፍስሐ

# ምን እንጠብቅ?

በታገል አልማው (መ/አ)

ኡደት ያመጣሽ አዙሮ
አንቺ የአመት ቀጠሮ
ምን ይዘሽ መጣሽ ዘንድሮ፤
በቢጫው የአደይ ቀለም
ምን እናስተጋባ ለአለም
ምን ይዘሽ መጣሽ መስከረም?
አመት ዙረሽ ቼ ብለሽ ነይ
ይፍካ ምድሩ ይልበስ ፀደይ፤
ከርመሽ ለመጣሽበት - ይወድቅልሻል ፍሪዳ
እንቁጣጣሽ እንላለን - ጮራዋን ቀድመን ማለዳ፤
የበዛ ቀን የበዛ ወር የደስታ አለም
ለሐበሻ ካንቺ በቀር ግዙፍ የለም
የወር ቀደምት ነሽ መስከረም፡፡
አንቺ የወራት ንጉስ ነገን ግለጪ በጥሩ እድል
በረከትሽ ይብዛልን ከከርሞሽም አንጉደል፡፡
የአባይም ህልሙ ይፍካ - ለሐበሻ ብርሃን ይሁን
በረከትሽ እጥፍ ይደግ - ፀጋሽ ይትረፍረፍልን፤
አመት የምንጠብቅሽ ከወራት ሁሉ የምትበልጪ
የተመረጥሺው መስከረም እባክሽ በረከት አምጪ
ብዕር ክዳን አውልቆ ከህፃናት እጅ ይውላል
ሰማይ ደመናን ገልጦ እንቡጥ አበባን ያፈካል፤
ይሔ ነው ሃድራሽ መስከረም
የተስፋ ስያሜሽ ትርጉም፤
አበባየሁሽ እያልን
ተስፋችን ላይ ናፍቆት ጥለን
እንቀበልሽ አጨብጭበን፡፡
አውዳመቷ መስከረም ሐበሻዊት ሰምና ወርቅ
አንቺ ንገሪን በቋንቋሽ ሲነጋ እንድንጠብቅሽ።




ካርቱን:- በሰለሞን ሁነኛው (ሻ/ቃ)

# ዕቅዳን በተግባር!!

በአባቱ ወልደማርያም (መ/አ)
የጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ ተስፋ፣ አዲስ ሞራል፣ አዲስ ዕቅድ የሚሰነቅበት ወቅት ነው አዲስ ዓመት። ባሳለፍነው 2017 ዓ/ም እንደ ግለሰብ ይሁን እንደ ተቋም አዲስ እቅድ ተግባራዊ ተደርጓል። በመሆኑም እቅዱን አሳክተነዋል ወይ? የሚለውን በዓመቱ መገባደጃ ላይ እንገመግማለን። እናም አሮጌውን 2017 ዓ/ም አጠናቀን ወደ አዲሱ 2018 ዓ/ም ተሻግረናል። ተቋማችንም በተለይ ካለፉት ስድስት ዓመታት ጀምሮ የመንግስትንና የህዝባችንን የዘመናዊ ሠራዊት ግንባታ ጥረትና ፍላጎት ስኬታማ ለማድረግ አቅዶ በሙሉ ኃይሉ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

ዋናው ጥረት ደግሞ ሠራዊቱ የተጣለበትን ሀገራዊ እና ህዝባዊ ተልዕኮ በብቃት እንዲወጣ በወታደራዊ ሳይንስና ጥበብ የተካነ አቅም መፍጠር ነው። ይህን በወታደራዊ ሳይንስና ጥበብ የተካነ ዘመናዊ ሠራዊት ለመገንባት ከወታደሩ እስከ ከፍተኛ የሠራዊቱ አመራር ድረስ ተግባር ተኮር ስልጠናዎችና ትምህርቶች እየተሰጡ ይገኛል።

ይህን የተቋሙ የዘመናዊ ሠራዊት ግንባታ እውን እንዲሆን ሀገራዊና ተቋማዊ ኃላፊነታቸውን በብቃት እየተወጡ የሚገኙ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶችንና ኮሌጆችን የሚመራው ደግሞ የመከላከያ ትምህርትና ስልጠና ዋና መምሪያ ነው።

በ2017 ዓ/ም መለያ ሎጎውን ተግባራዊ ያደረገው የመከላከያ ትምህርትና ስልጠና ዋና መምሪያ የራሱ ራዕይና ተልዕኮ አለው። የዋና መምሪያው ራዕይ በ2022 ዓ.ም በፕሮፌሽናል ሠራዊት ግንባታ ከአፍሪካ ሀገራት ቀዳሚና ተመራጭ የትምህርትና ስልጠና ተቋም ተገንብቶ ማየት ነው። ተልዕኮው ደግሞ የተቋሙን ተልዕኮ በላቀ ውጤት ለመወጣት የሚያስችል አመራር፣ ሙያተኛ እና ተዋጊ የሠራዊት አባላት ማፍራት እና ውጤታማ፣ ተወዳዳሪ የትምህርትና ስልጠና ሥርዓት እና ተቋም መገንባት ነው።

ዋና መምሪያው የ2017 በጀት ዓመት የስራ አፈፃፀም በ2017ዓ/ም ነሀሴ ወር አጋማሽ ላይ ከማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች አመራሮች፣ አሰልጣኞችና መምህራን ጋር በመከላከያ ጠቅላይ መምሪያ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ግምገማ አድርጓል።

ግምገማውን የመሩት የመከላከያ ትምህርትና ስልጠና ዋና መምሪያ ኃላፊ ሌተናል ጄኔራል ይመር መኮንን፣ ለአንድ ሀገር የዘመናዊ ሠራዊት ግንባታ ወቅቱን ያገናዘበና በእውቀት የታነፀ ሚዛናዊ ተዋፅኦ ያለው ፕሮፌሽናል ሠራዊት መገንባት የግድ ይላል። በተለይ ክፍለ ዘመናችን የቴክኖሎጂ ምጥቀትና ወታደራዊ ሳይንስ እድገት የታየበት እንዲሁም ዘመን አፈራሽ ወታደራዊ ቴክኖሎጂ የታጠቀ ዘመናዊ ሠራዊት የሚጠይቅ ዘመን ላይ ነን ብለዋል።

“በመሆኑም ወደ እዚህ ደረጃ ለመድረስ ደግሞ መጀመሪያ አንድ ወታደር ይሁን አመራሩ ማወቅ ያለበትን የውትድርና መሠረተ ሀሳቦች ማስያዝ ያስፈልጋል»። አሁን ላይ የአለማችንን የውትድርና እድገትን ከተቋማችን የእድገት ደረጃ ጋር ባናነፃፅርም ያለንን ውስን ኢኮኖሚያዊ አቅም ግምት ውስጥ ያስገባ ወታደራዊ ኃይል መገንባት ለሀገራችን የውዴታ ግዴታ ነው” ሲሉ ሌተናል ጄኔራል ይመር ገልፀዋል። ከዚህ አንፃር የመከላከያ ትምህርትና ሥልጠና ዋና መምሪያ ባቀደው እቅድ መሠረት የዘመናዊ ሠራዊት ግንባታን የሚያግዙ ስራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

በ2017 በጀት ዓመት የመከላከያ ትምህርትና ስልጠና ዋና መምሪያ ሁሉንም ማሰልጠኛዎችና ኮሌጆችን መምራት የሚችልበትን ዝርዝር እቅድ አዘጋጅቶ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። በዝግጅቱ ምዕራፍ የሰው ኃይል አደረጃጀትና የሥርዓተ ትምህርት መመሪያዎችን አሻሽሎ በማስተግበር ረገድ ውጤታማ ስራዎችን አከናውኗል። ዋና መምሪያው በየትምህርትና ሥልጠና ምዕራፉ ትምህርትና ስልጠናው በዕቅዱ መሰረት መከናወኑን ጥብቅ ክትትል እና ድጋፍ አድርጓል። ይህ በመሆኑም እንደ ተቋም የተሻለ ወታደራዊ አቅምና ብቃት ያለው ሠራዊት እንዲገነባ ተደርጓል።



ሌተናል ጄኔራል ይመር መኮንን
የመከላከያ ትምህርትና ስልጠና ዋና መምሪያ ኃላፊ

ፎቶ:- ከማህደር




ሌተናል ጄኔራል ይመር እንዳሉት በበጀት ዓመቱ በተለይ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶች “እያሰለጠንን እንዋጋለን!” በሚል መርህ የቀጠናቸውን ሠላም ከማፅናት ጎን ለጎን የግብርና ስራዎች አከናውነዋል። አብዛኛዎቹ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች ባሏቸው የተወሰነ መሬት ላይ ሰልጣኞቻቸውንና ተማሪዎቻቸውን በማሳተፍ የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬዎችን እንዲሁም አዝዕርቶችን በማልማት ለራሳቸው የምግብ ፍጆታ ማዋል ከጀመሩ ሰነባብተዋል፡ ፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ዶሮና ከብት በማርባትም በወተትና እንቁላል ምርት የሠልጣኞቻቸውና ተማሪዎቻቸውን ምግብና ደጉመዋል። ይህ በመደረጉ ሰልጣኙም ይሁን ተማሪው የተመጣጠነ ምግብ እየተመገቡ ደስተኛ ሆኖ ትምህርቱ ላይ ብቻ ትኩረት እንዲያደርግ አወንታዊ ሚና ተጫውቷል። ይህ ብቻም ሳይሆን ቀደም ሲል ለቀለብ ይወጡ የነበሩ ከፍተኛ ወጪዎችን በራስ አቅም እንዲሸፈን መደረጉን አብራርተዋል።

ሌላው ክፍሎች እንዲያከናውኑ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የተለያዩ ማ/ት/ቤቶችና ኮሌጆች በርካታ መሠረተ ልማቶችን አከናውነዋል። ካከናወኗቸው በርካታ መሠረተ ልማት ግንባታዎችና የጥገና ሥራዎች መካከል የአዛዥፐነትና ስታፍ ኮሌጅ ባለ 10 ወለል ህንፃ፣ የአዋሽ ውጊያ ቴክኒክ ትምህርት ቤት የተማሪዎች መኖሪያ ህንፃ፣ የጦላይ ከፍተኛ ባለሌላ ማዕረግ ማሰልጠኛ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግንባታ፣ የሜጀር ጄኔራል ሙልጌታ ቡሊ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የተማሪዎችና ስታፍ መመገቢያ፣ ማብሰያና መኖሪያ፣ የሁርሶ እጩ መኮንኖች መዝናኛ ክበብ ግንባታ ስራዎች በተቀመጠው እቅድ መሠረት የተሰሩና በመሠራት ላይ ያሉ ናቸው። በተለያዩ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆችም በርካታ የጥገና ስራዎች ተግባራዊ ተደርጓል። በ2018 በጀት አመትም የተጀመሩና ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን መቋጨት የሁሉም አመራር ትኩረት እንዲሆን ትዕዛዝ ተሰጥቷል። ከዚህ ሌላ አመራሩ ከዋና መምሪያው የሚሰጠውን የሥራ ኃላፊነት ብቻ ጠብቆ መስራት ብቻ ሳይሆን ከሚመለከታቸው የተቋሙ ባለድርሻና አጋር አካላት ጋር በመነጋገር ችግሮች እንዲፈቱ ማድረጋቸው የተቋማቱ አመራርና አባላት የዳበረ የስራ ተነሳሽነት እንዳላቸው ያሳያል።

የበጎ አድራጎት ስራን በተመለከተ በሁሉም ትምህርትና ስልጠና ተቋሞች ከመማር ማስተማር ጎን ለጎን የሠራዊታችንን እውነተኛ ህዝባዊነትን በተግባር አሳይተዋል።

ከተሰሩ የበጎ አድራጎት ስራዎች መካከል ጥቂቶቹን ብንጠቅስ የአቅመ ደካማ አርሶ አደሮችን ሰብል ከማረም ጀምሮ የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ፣ በአቅም ማጣት ምክንያት መማር ላልቻሉ ህፃናት የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፣ የአቅመ ደካማ ወገኖችን ቤት ማደስ ወዘተ ተጠቃሽ ናቸው። በእነዚህም በጎ አድራጎት ተግባራት የአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዲፈጠር ተደርጓል። ይህ የሠራዊቱና የማህበረሰቡ ቁርኝት ደግሞ ለአከባቢው አስተማማኝ ሠላም መረጋገጥ አወንታዊ ሚና አለው። የአከባቢው ሠላም አስተማማኝ ሆነ ማለት ደግሞ የመማር ማስተማሩ ሂደት ሠላማዊ እንዲሆን ያስችለዋል። ዋና መምሪያው በ2017 በጀት ዓመት ከትምህርትና ስልጠና ውጭ ሁሉም ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች በግብርና፣ አዳዲስ መሠረተ ልማት ግንባታዎችና ጥገናዎች እንዲሁም የበጎ አድራጎት ስራዎች የነቃ ተሳትፎ በማድረጋቸው ከጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ሽልማት ተበርክቷል።

እንደ ወታደር ብዙ ፈተናዎችን መቋቋም መሰረታዊ የተቋማችን ቁልፍ እሴት ነው። እናም ማሰልጠኛዎች አሁን ባለው የፀጥታ መደፍረስ ምክንያት ድርብ ኃላፊነትን እየተወጡ በመሆኑ በቀጣይም በስልጠና ላይ እንቅፋት የሚፈጥሩ መሰናክሎችን በማስወገድ የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ ተቋማዊ ተልዕኮ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ነው ጄኔራል መኮንኑ ያመለከቱት። ከህግ ማስከበርና ሠላምን አጽንቶ ከማዝለቅ ሥራዎች ጎን ለጎን በማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች አንድነትን የሚያጠናክሩ ተግባራት ላይ በልዩ ትኩረት እንዲከናወን አሳስበዋል። በተለይ የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በህግና አሠራር ብቻ በመፍታት ሠራዊቱ በማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች ላይ ያለውን አመኔታ እንዲጎለብት ማድረግ ይገባል ካሉ በኋላ ህግና አሰራርን የማይተገብር አመራርም ይሁን አባል ላይ የተጠያቂነት አሰራር ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

ሌላው በሁሉም ማሰልጠኛዎችና ኮሌጆች ትምህርትና ስልጠናዎችን በተሻለ ለመስጠት የሰው ሰራሽ አስተውሎ ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ በግምገማው ወቅት ተነስቷል።

ሰው ሠራሽ አስተውሎት (Artficial Inteligence) (AI) ማለት ደግሞ የመጪው ትውልድ ቴክኖሎጂ ነው። በመሆኑም የመከላከያ ትምህርትና ስልጠና ዋና መምሪያ በ2018 በጀት ዓመት ስልጠናዎችን በሠው ሰራሽ አስተውሎ ለመጀመር ቆርጦ ተነስቷል። ክፍሉ በሠው ሰራሽ አስተውሎ ስልጠናዎችን እና ትምህርቶችን ለመስጠት ማቀዱ የሠው ኃይልና በጀት ቅነሳ እንዲሁም የስልጠና እና ትምህርት ጥራት ላይ አወንታዊ ሚና እንደሚጫወት ታምኖበታል።

እንደ ሀገር እንኳን ብንመለከት ኢትዮጵያ በ2012 ዓ.ም የኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩትን በማቋቋም በዘርፉ ከአፍሪካ ቀዳሚ ለመሆን እየሰራች ትገኛለች።

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥርዓተ ትምህርት ተቀርፆለት ተማሪዎች እየተማሩበት መሆኑ እንዲሁም የአምስት ሚሊዮን ኮደሮች ስልጠና እየተሰጠ መሆኑ ኢትዮጵያ ለዘርፉ የሰጠችው ትኩረት ከፍተኛ እንደሆነ ሌተናል ጄኔራል ይመር መኮንን አንስተዋል።

ሰው ሰራሽ አስተውሎት ተስፋዎችና ስጋቶች እንዳሉት ቢነገርም የሰዎችን ድካም በመቀነስና አኗኗርን በማቅለል የተሰጠውን ስራ በአጭር ጊዜ ለማከናወን የሚረዳ ቴክኖሎጂ እንደሆነና ከስጋቱ ይልቅ የሚያስገኘው ጥቅም ከፍ ያለ እንደሆነ ይነገራል።

በመሆኑም በመከላከያ ትምህርትና ስልጠና ዋና መምሪያ ስር በሚገኙ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች ከዚህ በፊት አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ ሲሙሌተሮች እንደተጠበቁ ሆነው ስልጠናዎችንና ትምህርቶችን የዘመኑ ቴክኖሎጂ በሆነው የሰው ስራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ ለመጠቀም አሰልጣኙንም ሆነ መምህሩን ከቴክኖሎጂ ጋር በሚገባ ለማላመድ ዋና መምሪያው የ2018 በጀት ዓመት ቁልፍ የሥራ እቅዱ አድርጓል።

ዋና መምሪያው በሰው ሠራሽ አስተውሎ ቴክኖሎጂ ብቻ ሳይወሰን ሁሉም ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች ለተቋሙ ሁለንተናዊ እድገት የሚረዱ የምርምር እና ጥናት ስራዎች ላይ አመራሮች ሚናቸውን በላቀ ብቃትና ኃላፊነት ስሜት እንዲወጡም ሌተናል ጄኔራል ይመር አሳስበዋል።

ምክንያቱም “አሁን ላይ አለም ተገማችንና ኢ ተገማች የሆኑ ክስተቶች የሚስተናገድበት ወቅት ላይ እንገኛለን ያሉት ሌተናል ጄኔራል ይመር አዲሱ 2018 ዓ.ም ትናንትን፣ ዛሬንና ነገን አስተሳስሮ የተቀናጀ ጥረት በማድረግ ለተቋሙ የላቀ ሁለንተናዊ ዝግጁነት ሁሉም አመራርና አባላት በቁርጠኝነት መረባረብ ይገባል” ሲሉም አፅንኦት ሰጥተው አሳስበዋል።

በ2018 በጀት ዓመት ዋና መምሪያው የተሻለ የሥራ አፈፃፀም ለማስመዝገብ የሚያስችለውን ዝርዝር ዕቅድ ላይ ውይይት ከተደረገበት በኋላ የአፈፃፀም አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ጥሩ የስራ አፈፃፀም ለነበራቸው ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች እንዲሁም ጥሩ የሥራ አፈፃፀም ላላቸው በጡረታ በክብር ለተሰናበቱ አባላትና አመራሮች የማበረታቻ ሽልማት በማበርከት ዓመታዊ የስራ አፈፃፀም ግምገማው በስኬት ተጠናቋል።

በአጠቃላይ የመከላከያ ትምህርትና ስልጠና ዋና መምሪያ በ2017 በጀት ዓመት በስሩ የሚገኙ የትምህርትና ስልጠና ተቋማትን በቴክኖሎጂ አዘምኖ ወቅቱን በዋጀ ሥልጠናና ትምህርት በእውቀት፣ በአስተሳሰብና በችሎታ የዳበረ ፕሮፌሽናል ሠራዊት ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት አሳክቷል።

2018 ዓመተ ምህረት የሠላም የደስታ እና የእድገት ዓመት ይሁን! ሠላም!!!



ፎቶ፦ በፉራ አብደላ (መ/አለቃ)

አዲሱ የባህር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ህንፃ

# ባህር ኃይላችን በአዲስ ምዕራፍ

በአደም አሊ (መ/አ)
የጋዜጣው ሪፖርተር

የኢትዮጵያ ባህር ኃይል ታሪክ የሚጀምረው ከ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ከጥንታዊው የአክሱም ሥልጣኔ ዘመን ጀምሮ ስለመሆኑ ታሪክ ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጂ በተለያዩ ምክንያቶች ኢትዮጵያ ከባህር ዳርቻዎች እርቃ ቆይታለች። የባህር ኃይሏም ፈርሷል፡፡ የባህር በሩም ይሁን የባህር ኃይል ግን ለኢትዮጵያ እጅግ አስፈላጊዎች ነበሩ፡፡ ከዓመታት በኋላ እንደገና እንዲደጅ ጥረት ተደርጎ ዳግም እውን መሆን ችሏል፡፡ እኛም የኢትዮጵያን የባህር ኃይል ታሪካዊ ጉዞን ከምስረታው እስከ መፍረስና መልሶ መደራጀቱን በተመለከተ የባህር ኃይል ምክትል አዛዥ ለውጊያ ድጋፍ አገልግሎት ከኮሞደር ተገኝ ለታ ጋር ያደረግነውን ቆይታ ከታሪካዊ መረጃዎች ጋር አቀናጅተን እንደሚከተለው አዘጋጅተናል፡፡ መልካም ንባብ፡-

የኢትዮጵያ ባህር ኃይል የተመሰረተው በ1948 ዓ.ም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ-መንግሥት ነበር። የባህር ኃይሉ የተደራጀውም ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ተቀላቅላ ኢትዮጵያ እንደገና የቀይ ባህር ዳርቻዋን በማግኘቷ ነበር። ይህ ክስተትም ለሀገራችን ትልቅ ስትራቴጂካዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድሎችን ይዞ የመጣ ነበር። የባህር ኃይሉ ሲቋቋም “የኢትዮጵያ ሮያል ባህር ኃይል” ተብሎ ይጠራ እንደነበር ያብራሩት ኮሞደር ተገኝ ለታ የሀገር ሉዓላዊነትን ማስከበር፣ የኢኮኖሚ ጥቅሞችን ማስጠበቅ የሚሉና ሌሎችንም ዓላማዎች ይዞ መቋቋሙን አንስተዋል፡፡

በ1966 ዓ.ም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከስልጣኑ ከወረደ በኋላ የሀገሪቱ የፖለቲካ አቅጣጫ ወደ ሶሻሊስት ጎራ ማዘንበሉን ተከትሎ የባህር ኃይሉም ከምዕራባውያን ይልቅ ከሶቭየት ህብረት ጋር ያለውን ግንኙነት አጠናከረ። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የባህር ኃይል መኮንኖችና ሙያተኞችንም ማፍራት ቻለ፡፡ ሶቭየት ህብረትም በወቅቱ በአሰብና በዳህላክ ደሴቶች ላይ የባህር ኃይል ማዕከላትን በማቋቋም የቀጠናውን ፖለቲካ ለመቆጣጠር የኢትዮጵያን ወደቦች እንደ ቁልፍ ስትራቴጂካዊ አማራጭ ትጠቀም እንደነበር ታሪክ ያስረዳናል፡፡

በወቅቱም የባህር ኃይሉ በመርከብ ብዛት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ እንደነበርም ይነገራል። ይሁን እንጂ በኤርትራ በኩል የትጥቅ ትግል በመኖሩ ምክንያት የባህር ኃይሉ ከባድ ፈተና ውስጥ ገብቶ ነበር። ሁሉም የባህር ኃይል ማዕከላት ኤርትራ ውስጥ መገኘታቸው ደግሞ በቀጥታ የግጭቱ ሰለባ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ በወቅቱም የምፅዋ ወደብ በኤርትራ ኃይሎች ቁጥጥር ስር መዋሉ ለባህር ኃይሉ ትልቅ የሞራልና የሎጂስቲክስ ኪሳራን አስከትሎበት ነበር። በዚህም የተነሳ የባህር ኃይሉ ዋና መሥሪያ ቤት ወደ አዲስ አበባ እንዲዛወር መደረጉን ታሪክ ይጠቁማል።

በወቅቱ የነበረው መንግስትም ትኩረቱን በመደበኛው ጦርና በአየር ኃይሉ ላይ ብቻ በማዋሉ የባህር ኃይሉ አቅም የበለጠ ሊዳከም ቻለ። በአንድ ወቅት በምስራቅ አፍሪካ ጠንካራ ከሚባሉት አንዱ የነበረው የኢትዮጵያ ባህር ኃይልም ቀስ በቀስ ተዳክሞ ለመውደቅ ተቃረበ፡፡ በ1983 ዓ/ም የደርግ መንግሥትን መወደቅ ተከትሎ ኤርትራ ከተገነጠለች በኋላ ኢትዮጵያ በድጋሚ ወደብ አልባ ሀገር ሆነች። ይህ ክስተት ደግሞ ለኢትዮጵያ ባህር ኃይል የመፍረሱ የመጨረሻ ምክንያት ሆነ። በዚህም ወደብ አልባ በሆነች ሀገር ውስጥ የባህር ኃይልን ማስቀጠል የማይቻል ሆነና እስከ ቅርብ ጊዜያት ድረስ ሀገራችን ባህር ሀይል የሌላት ሀገር ሆና ቆየች።

የባህር ኃይሉ መርከቦችም ለተወሰነ ጊዜ በየመንና በጅቡቲ ወደቦች ተጠልለው ቢቆዩም ዘላቂ መፍትሄ መሆን ግን አልቻለም። ኢትዮጵያ ከአዲሱ የኤርትራ መንግሥት ጋር በአሰብ ወደብ ለመጠቀም የሊዝ ስምምነት ለማድረግ ብትሞክርም ጥያቄው ተቀባይነት ማግኘት አልቻለም። በመጨረሻም በ1988 ዓ/ም ለጅቡቲ መንግሥት ያልተከፈለ የወደብ ኪራይ እዳን ምክንያት በማድረግ ቀሪዎቹን የጦር መርከቦች በመሸጥ የኢትዮጵያ ባህር ኃይል በይፋ እንዲፈርስ ተደረገ። ከባህር ኃይሉ መፍረስ ጋር ተያይዞም በሺዎች የሚቆጠሩ ከፍተኛ ሥልጠና የወሰዱና የካበተ ልምድ ያላቸው የባህር ኃይል አባላት ያለክብር ተበትነዋል። የእነዚህ ሙያተኞች እውቀትና ልምድ ለሀገር ሳይጠቅም መባከኑ በራሱ በሀገር ላይ ትልቅ ኪሳራን አስከትሏል። ከዚህም በተጨማሪ የባህር ኃይሉ መፍረስም በሀገር ላይ የሚከተሉትን ጉዳቶች ማስከተሉን ኮሞደር ተገኝ ለታ ተናግረዋል፡፡

- **ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ**፡- ኢትዮጵያ የራሷ የባህር በር ባለቤት ባለመሆኗ የውጭ ንግዷ ሙሉ በሙሉ በጅቡቲ ወደብ ላይ ጥገኛ እንድትሆን አድርጓታል፡፡ ይህም ለወደብ አገልግሎት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እንድታወጣ አስገድዷታል። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በርካታ የገቢና ወጪ ንግዷን የምታከናውነው በጅቡቲ ወደብ በኩል ነው፡፡ ለዚህም በዓመት በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ታወጣለች። ይህ ከፍተኛ ወጪም የሀገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት በእጅጉ ጎድቷል።
- **የደህንነት ሥጋት**፡- የባህር ኃይል አለመኖር በቀይ ባህር አካባቢ የሚከሰቱ የደህንነት ሥጋቶችን፣ በተለይም የባህር ላይ ወንብድናን፣ ህገ-ወጥ የሰዎችና የጦር መሳሪያ ዝውውርን ለመከላከል የነበረውን አቅም አሳጥቷል።
- ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ችግር፡- የባህር ኃይል አለመኖር ኢትዮጵያ በቀይ ባህርና በአፍሪካ ቀንድ ፖለቲካ ላይ ያላትን ተጽዕኖ በእጅጉ ጎድቷል። በባህር ዙሪያ በሚደረጉ ዓለም አቀፍዊ ውሳኔዎችና ስምምነቶች ላይ ያላት ተሳትፎና ድርሻ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ ሆኗል።

**ሥነ-ልቦናዊ ተጽዕኖ**፡- የባህር ኃይሉ መፍረስ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ትልቅ ሀገራዊ ኪሳራን አስከትሏል። በርካታ አሉታዊ ተጽዕኖዎችንም አሳድሯል። ስለሆነም የባህር ኃይሉ መፍረስ አልነበረበትም ያሉን ኮሞደር ተገኝ ለታ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የውሀ ሀብት ያላት ሀገር እንደ መሆኗ የባህር ኃይል የማስፈለጉ ጉዳይም አጠያያቂነት አልነበረውም ብለዋል፡፡ ከሦስት አስርት ዓመታት በላይ ተበትኖ የነበረው የኢትዮጵያ ባህር ኃይል እንደገና እንዲቋቋም የተወሰነው በ2011 ዓ/ም ከሀገራዊ ለውጡ ማግስት ነው። ይህ ውሳኔም በብዙዎች ዘንድ አስደናቂና ታሪካዊ የተባለ፣ የኢትዮጵያን የባህር ላይ ምኞት እንደገና ያቀጣጠለ ክስተትም ነበር።

የባህር ኃይል መቋቋሙ ከቀድሞው የባህር ኃይል ዓላማዎች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውና አሁን ካለው የሀገሪቱና ቀጠናዊ ሁኔታዎች ጋር የተጣጣመ ነው፡፡ አሁን ላይ የኢኮኖሚ ጥገኝነትን መቀነስ፣ የቀጠናውን ሰላምና ደህንነት ማረጋገጥ፣ የሀገራዊ ክብርን መመለስ በሚሉት ጉዳዮች ላይም ትኩረቱን አድርጎ እየሰራ መሆኑን ምክትል አዛዡ ይናገራሉ፡፡

የባህር ኃይሉ መልሶ መቋቋምም የመከላከያ ሰራዊቱን ሙሉ የሚያደርግና የሀገሪቱን ሉአላዊነት በሁሉም አቅጣጫ እና አወድ ለመጠበቅ የሚያስችል ነው፡፡ ከተቋቋመ በኋላም በተለያየ መልኩ የማደራጀት ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በምስረታው ወቅትም ልምድ ያላቸው የቀድሞ የባህር ኃይል መኮንኖችና አባላት በክብር ተጠርተው ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ አዳዲስ አባላት በሀገር ውስጥ ባሉ ማሰልጠኛዎች ተገቢ ስልጠና እንዲወስዱ የማድረግ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ እየተሰሩም ይገኛሉ፡፡ ከውጭ ሀገራት በተገኙ የስልጠና እድሎች አማካኝነት የአጭርና የረዥም ጊዜ ስልጠናዎችን ወስደው አስፈላጊውን ብቃት የጨበጡ ሙያተኞችም በርካቶች ናቸው፡፡ በዚህም የሰው ኃይልን የማብቃት፣ የአመራሩንና የተዋጊ ኃይሉን የማደራጀት ስራዎች በጥራት ተከናውነዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ባህር ኃይል በድጋሚ ከተቋቋመ ጥቂት ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥም በርካታ ተስፋ ሰጪ ስራዎችን አከናውኗል። በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወጣውን ደንብና መመሪያ መሰረት በማድረግ የተለያዩ መመሪያዎች፣ ህጎችና ማንዋሎች ተዘጋጅተው ስራ ላይ መዋላቸውንም ምክትል አዛዡ አብራርተዋል፡፡ የስልጠና ካሪኩለሞች ተዘጋጅተው በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ እየተሰጡም ነው፡፡ ዛሬ ላይ የባህር ኃይሉ አጠቃላይ ቁመና እየተላበሰ ይገኛል፡፡ የጀመራቸውን ስራዎች በቀጣይም የበለጠ አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በተለይም የባህር ኃይሉ ዋነኛ አላማ የኢትዮጵያን የባህር ላይ ጥቅም ማስከበር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተሻለ አቅም እንዲፈጥር ማድረግ ተችሏል፡፡

በባህር ላይ የሚከሰቱ ማንኛውም አይነት ግጭቶችን መከላከልና የሀገሪቱን የንግድ መርከቦች ደህንነት ማረጋገጥ የባህር ኃይሉ ኃላፊነት መሆኑንም ተናግረዋል፡፡ በተጠናቀቀው በጀት ዓመትም በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች በህብረተሰባችን ላይ ተከስተው በነበሩ የጎርፍ አደጋዎችን ላይ ፈጥኖ በመድረስ የህብረተሰባችንን ህይወትና ንብረት የመታደግ ስራዎችን ሰርቷል፡፡ ከሰራዊታችን ጎን በመሆንም የሚሰጡትን ማንኛውንም ግዳጆች በብቃት ተወጥቷል፡፡ እየተወጣም ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የባህር ኃይሉን አቅም መገንባት፣ የአካባቢውን ደህንነትና የባህር ዳርቻን ጥበቃ ማረጋገጥ እንዲሁም ከሌሎች ሀገራት ጋር በመተባበር የጋራ ስራዎችን መስራት የባህር ኃይሉ የወደፊት እቅዶች መሆናቸውንም ገልፀዋል፡፡

በቀጣይም በአዲሱ በጀት ዓመት የጀመርናቸውን የሰው ኃይል የማብቃት፣ የማደራጀትና የማጠናከር ስራዎችን በተሻለ መልኩ እንሰራለን ያሉት ም/አዛዥ ኮሞደር ተገኝ በተለይም ዋናው ስራ የሰው ኃይልን ማብቃት በመሆኑ ሙያተኞችን በማሰልጠንና አቅሙን በማሳደግ ላይ በትኩረት እንደሚሰራ ተናግረዋል፡፡ ለዚህም አዲስ የተገነባው ዋና መስሪያ ቤትና የስልጠና ማዕከል ስራዎችን በተደራጀና በዘመናዊ መንገድ ለመስራት የሚያግዝ መሆኑንም አረጋግጠዋል፡፡ የተቋማችን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከሀገሪቱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ተከባብረንና ተባብረን የሀገራችንን ጥቅም ባስከበረ መልኩ ስኬታማ ስራዎችን ለመስራ መዘጋጀታቸውን አብራርተዋል፡፡

የባህር ኃይልን የመገንባት ሂደት ከፍተኛ ሀብትና የረጅም ጊዜ ስራን የሚጠይቅ እንጂ በአንድ ጀምበር የሚጠናቀቅ ስራ አይደለም ያሉት ምክትል አዛዡ ተቋሙን በማጠናከር በኩል የሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን ጠቁመዋል። ወጣቱ ትውልድ ተቋሙን በመቀላቀልና በሌሎች መንገዶች ድጋፍ በማድረግ ሀገራዊ ኃላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባውም አሳስበዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአዲሱ የ2018ዓ/ም በጀት ዓመት የጀመርናቸውን የሠላምና የማረጋጋት ስራዎች አጠናክረን የምንቀጥልበት፣ ተጨማሪ ድሎችን የምናስመዘግብበትና ህዝባችንም ወደ ሰላማዊ ኑሮው የሚመለስበት ዓመት ይሆን ዘንድ መልካም ምኞታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በአጠቃላይ የባህር ኃይሉን በማደራጀት በኩል እየተሰራ ያለው የተቀናጀ ስራ ውጤታማ ነው፡፡ ለሀገርና ለህዝብ የኩራት ምንጭ እንዲሆን ተደርጎም እየተደራጀ ነው፡፡ ለዚህም በተቀናጀ መልኩ የተከናወኑ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የባህር ኃይላችን በስኬት የታጀበ ስራም የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል መልዕክታችን ነው፡፡ ሰላም

# የውጊያ ድጋፍ አቅሞቻችን

በማሙሸት ከደነው (መ/ለ)
የጋዜጣው ሪፓርተር

እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሠላም አደረሳችሁ! አዲስ ዓመትን ሀገርና ህዝብ በአዲስ መንፈስ፣ በአዲስ ዕቅድና በአዲስ ተስፋ ይቀበሉታል፡፡ ከአሮጌው ዘመን በመማር ለአዲሱ ዓመት የተለያዩ ዕቅዶችን ያወጣሉ ። መልካም ነገሮችን ይዘው ይነሳሉ ። በአዲሱ ዘመን ስኬታማ ተግባራትን ለማከናወን በአዲስ መንፈስ መነሳቱም ተለምዷዊ ነው፡፡

ጀግናው የሀገር መከላከከያ ሠዊታችንም ከህዝብ አብራክ ወጥቶ ህዝቡን እያገለገለ ኢትዮጵያን በመስዋዕትነቱ እያፀና ከዘመን ዘመን ይሻገራል፡፡ እምዬ ኢትዮጵያን በውስጡ አርግዞ ከአሮጌው ዓመት ወደ አዲሱ ዓመት የተለያዩ እቅዶቹን አንግቦ ብቅ ይላል፡፡ ‹‹ጎሽ ለልጇ ስትል ተወጋች›› እንዲሉ አባው፣ ሠራዊታችንም ስለ ኢትዮጵያ ሲል ብዙ ዋጋ እየከፈለና ፈተናዎችን እያለፈ ለአዲሱ ዓመት ለ2018 ደርሷል፡፡

ተቋሙ በህገ- መንግስቱ የተሰጡትን ተልዕኮ በፅናትና በቁርጠኝነት እየፈፀመ ነው፡፡ እንዲሁም የአሰራር ለውጥ በማድረግ ዘመናዊና ዘመን ተሻጋሪ ስራዎችን እየሰራም ይገኛል ። በ2017 በጀት ዓመትም ዘርፈ ብዙ ስራዎችን ሲከውን መምጣቱ እሙን ነው፡፡ በዚህ ተግባሩም ተቋሙን ብሎም ሀገርን የሚያኮራ ተግባሮችን አከናውኗል፡፡ የ2018 አዲስ ዓመትን በማስመልከት ‹‹ጋሻ ጋዜጣ›› ባዘጋጀችው ልዩ ዕትም የሠራዊታችን ክፍሎች በ2017 በጀት ዓመት ሲሰሯቸው የመጡትን አኩሪ ተግባራት እና ለሠራዊታችን ያላቸውን የአቅም ግንባታ ሚና በጥቂቱ ለማስቃኘት የወደድኩበት መሰናዶ ነው፡፡ መልካም ንባብ!

በበጀት ዓመቱ በርካታ ስራዎች በመስራት ለሠራዊታችን የአቅም ግንባታ ስራን፣ በመደገፍና ተቋሙ የያዘውን ራዕይ ለማሳካት ጥረት በማድረግ ውጤታማ ስራዎች በመስራት ላይ ከሚገኙ ክፍሎች መካከል የመከላከያ መሃንዲስ ዋና መምሪያ ተጠቃሽ ነው ። ዋና መምሪያው በ2017 በጀት ዓመት በርካታ ስራዎችን አከናውኗል፡፡ ያከናወናቸውን ዘርፈ ብዙ ስራዎች የዋና መምሪያው የስነ ልቦና ግንባታ ቡድን አድርሶናል፡፡ ይህንንም ለጋሻ ጋዜጣ በሚመች መልኩ በጥቂቱ እንዳስሳለን ።

የመከላከያ መሀንዲስ ዋና መምሪያ ከማንኛውም ጊዜ በላይ ብቁ ኢንጂነሮችን በማፍራት በራስ ችሎታ በአጭር ወራቶች እስከ G+4 የመስራት አቅምን እያሳደገ እና ፕሮጀክቶችን በፍጥነትና በጥራት እየሰራ ይገኛል፡፡

የውሃ ቁፋሮን አቅም ለማሳደግ የተገዙ ማሽኖችን ከውጭ በመጡ ሞያተኞች የስራ ላይ ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ የወስጥ አቅምን የመገንባት ስራ ሰርተዋል፡፡ ድሬዳዋ ለሠራዊት የጋራ መኖሪያ ቤት 20 ብሎኮችን ሠርቶ ማጠናቀቅ፤ የባህር ኃይል ዋና ቢሮ ከተያዘለት ዓመት በፊት ቀድሞ በመጨረስ በጥራትና በፍጥነት መስራት፤ ሌላው የዋና መምሪያው የብቃት ማደግና መጨመር ማሳያ ነው፡፡ በተቋራጭ ተይዘው የነበሩ ፕሮጀክቶችንም በራስ አቅም ለመስራት እና ፕሮጀክቶቹ ተጠናቀው ለሠራዊቱ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የተሰራው ስራ በጣም ጥሩ የሚባል ነው፡፡ የጎዴ ፕሮጀክትን በአጭር ጊዜ አጠናቆ ጨርሷል፡፡ ተጀምረው የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን በሚቀጥሉት ወራቶች ተጠናቀው ለአገልግሎት እንደበቁ ከዋና መምሪያው ያገኘነው መረጃ ይነግረናል፡፡

የፈንጅ መመርመሪያ መሳሪያ አዲስ በመግዛት እና መሳሪያውን ለዕዞችና ለተዋጊ መሃንዲስ ክፍለ ጦር አባላት ከውጭ በመጡ ሙያተኞች በማሰልጠን በመሳሪያው ላይ በቂ እውቀት እንዲፈጠር ተደርጓል፡፡ የመሀንዲስ ሞያተኞች፣ በአትሚስ (ሠላም ማስከበር) ግዳጅ የነበረች አሃዱን ለማውጣት የተሰማሩ አባላት የፈንጅ ፍተሻ እያደረጉ ሻለቃዋን ያለምንም እንቅፋት ወደ ሃገር ቤት እንድትገባ የተደረገው ስራ በጣም አኩሪ ስራ የተሰራበት ነበር፡፡ ከሌሎች የፀጥታ አካላት ጋር በመሆን በሀገር ውስጥ የሚቀሳቀሱ ፀረ ሠላም ኃይሎችን በመደምሰስ እና ለህዝብ ሠላምን ከማስፈን አኳያም ስራዎች ተሰርተዋል ።

የሠራዊቱን ኑሮ ለማሻሻል በሚደረጉ ስራዎች በሙሉ አቅም በመስራት የጊዜያዊ መጠለያ፣ የጄኔሬተር ጥገና እና መሰል ተግባራት ተከውነዋል ። አዲስ የሚጀመሩ ፕሮጀክቶችን በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ ግንባታቸውን ጀምሮ በማጠናቀቅ ለተጠቃሚ እንዲደርሱ ተደርጓል ። በራስ አቅም ለሚከናወኑ የግንባታ ስራዎች ግብዓት የሚሆኑ ብሎኬት ለማምረትና ከገበያ ላይ መግዛትን ለማስቀረትና በራሱ ለማምረት፤ ስሚንቶ ማዋሃጃ ሚክሰር እና ማሽን እንዲሁም ጠጠር ማምረቻ ክሬቸር በመግዛት ፕሮጀክቶችን ለመደገፍ እየተሰራ ነው ። በተጨማሪም ሠራዊቱን በምግብ ለመደገፍ እንደተቋም እየተካሄደ ባለው የልማት ስራዎች የተጀመረውን ለማጠናከርና ይበልጥ ለመስራት ሁለት የእርሻ ትራክተሮች ተገዝተው ገብተዋል፡፡

በጃንሜዳ ግቢ ውስጥ የተለያዩ የፍራፍሬ ችግኞችን የመትከል እና የመንከባከብ ስራዎች እየተሠራ ነው ። በዚህም አብዛኛው ፀድቆ ጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የወተት ላሞችን በመግዛትና በማርባት ለሠራዊቱ ጥራት ያለው ወተት በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረበ ሠራዊቱን የመደጎም ስራዎች በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ንብ የማነብና ዶሮዎችን የማርባት ስራዎች እየተሰሩ ሲሆን እንቁላል ለሠራዊቱ በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ እንዲጠቀም የማድረግ ስራዎች እየተከናወኑ ነው፡፡ ዋና መምሪያው ባከናወናቸው የግብርና ስራዎችም ከመከላከያ ፋውንዴሽን የማበረታቻ የእውቅና የምስክር ወረቀት አግኝቷል ።

ሠራዊታችን በጉልበቱ፣ በእውቀቱ፣ እና በገንዘቡ አቅመ ደካማ ወገኖችን መርዳት የተለመደ ህዛባዊ ባህሪው ነው፡፡ የመሃንዲስ ዋና መምሪያም በበጀት ዓመቱ ለማህበረሰቡ ድጋፍ አድርጓል፡፡ ድጋፍ ካደረጋቸው ስራዎች መካከል በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ የአቅመ ደካማ የህብረተሰብ ክፍሎች የወረዳው አመራሮች ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ባቀረቡት መሰረት ለ04 አባዎራዎች በ24 ቀናት ውስጥ አራት ቤቶችን በመገንባት ለተጠቃሚዎች ማስረከብ ተችሏል፡፡ በወለንጭቲ ከተማ ቦሰት ወረዳ የድልድይ ጥገና እና የጎርፍ መከላከያ በመስራት ለከተማ አስተዳደሩ ርክክብ ተደርጓል፡፡ በአዋሽ አርባ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 12 ብሎክ ቤቶችን በመገንባት ለሲቪል ማህበረሰብ ድጋፍ ተደርጓል ። በነቀምት የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ 06 ክፍሎችን በመገንባት ለማህበረሰቡ ርክክብ ተደርጓል፡፡ ቢሾፍቱ ለ15 አባወራና እማ ወራዎች የቀበሌ ቤት ግንባታ እና በማህበር ለተደራጁ ሴቶች 60 የእንጀራ መጋገሪያ ምጣድ የሚይዝ ሼድ ገንብቷል፡፡ ድሬዴዋ ሮቃ ለሃብሩ ወረዳ 240 ሜትር ጥልቅ ውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ የተቆፈረ ሲሆን በገንዘብ ሲተመን ከ50 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ መሆኑን ከዋና መምሪያው ያገኘነው መረጃ ይነግረናል ።

የመከላከያ መሀንዲስ ዋና መምሪያ በበጀት ዓመቱ የሰራቸው ስራዎች በርካታ ናቸው፡፡ ከላይ የዳሰስናቸው ከብዙ በጥቂቱ ነው፡፡ የተሰሩ እና እየተሰሩ የሚገኙ ስራዎች ለሠራዊታችን ያላቸው ድጋፍ ምትክ የማይገኝለት ነው፡፡

ሌላው በዚህ ልዩ ዕትም ማንሳት የፈለግነው የመከላከያ የጤና ዋና መምሪያን ነው፡፡ ሠራዊታችን ዳገት ቁልቁለቱን ወጥቶ ወርዶ፣ ብርዱን ሀሩሩን ተቋቁሞ ሀገርን ከጠላት የሚጠብቀው ጤንነቱ የተጠበቀ ሲሆን ነው፡፡ የሀገሬ ሰው በጨዋታ መሃል ‹‹ዋናው ጤና ነው›› ይላል፡፡ ጤና ከምንም በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን ሀገር ያወቀው ፀሀይ የሞቀው ሃቅ ነው፡፡ ተቋሙም ጤናው ያልተጠበቀ ሠራዊት የተሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ ሊወጣ እንደማይችል ጠንቅቆ ይገነዘባል፡፡ ስለዚህ የሠራዊቱን ጤንነት በተመለከተ በትኩረት በመስራት አካላዊና አዕምሮዓዊ ዝግጁነቱ የተሟላ እንዲሆን እያደረገ ይገኛል፡፡ እኛም በልዩ ዕትማችን የመከላከያ የጤና ዋና መምሪያ በበጀት ዓመቱ ከሰራቸው ዘርፈ ብዙ ስራዎች መካከል የዋና መምሪያው የስነ ልቦና ግንባታ ቡድን ያደረሰንን መረጃ በጥቂቱም ቢሆን ወደ እናንተ እናደርሳለን ።

የመከላከያ የጤና ዋና መምሪያ ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን በመከላከል ጥራት እና ተደራሽነትን

ወደ ገፅ 9 ዞሯል



ፎቶ፡- ከማህደር

በድሬዳዋ ከተማ በመከላከያ መሀንዲስ ዋና መምሪያ የተገነባው የጋራ መኖሪያ ህንፃ

# ሌተናል ጄኔራል ዘውዱ በላይ የማዕከላዊ ዕዝ አዛዥ መልዕክት

የተከበራችሁ መላው የዕዛችን አመራርና አባላት እንዲሁም ሲቪል ሰራተኞች በቅድሚያ እንኳን ለ2018 አዲስ ዓመት በሠላም አደረሳችሁ አደረሰን፡ ፡

ዕዛችን ዳሎል ማዕከላዊ ዕዝ ባሳለፍነው 2017 በጀት ዓመት በተሰማራበት የግዳጅ ቀጠና ሰላምን የማስከበር አንድነትን የማፅናትና ነፃነትን እውን የማድረግ ሃገራዊ ተልዕኮውን በብቃት ፈፅሟል ። ዕዙ በሰፊ ቀጠና ላይ ስምሪት በመውሰድ ውጣ ውረድ ሳይበግረው የአሸባሪዎችን አከርካሪ በመስበር ሰላም ለተጠሙት ዜጎች የድል ዜና አብስሯል ፤ ህገ-መንግስታዊ ግዳጁንም በጀግንነት ተወጥቷል ።

በሁኔታ መሃል ተፈጥሮ ከግጭት ሳይላቀቅ ዓመታትን ያስቆጠረው ማዕከላዊ ዕዝ በ2017 በጀት ዓመት ተበታትነው በየስርቻው የተደበቁ የጥፋት ሃይሎችን በማደንና እዚህም እዚያም የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ማረጋጋት ችሏል፡ ፡ ህዝብና ሰራዊቱን የሚያቀራርቡ ስራዎችን በመስራት የጋራ መድረኮችን ፈጥሮ በማወያየትና ግልፅ ግንዛቤ በመፍጠር በፍፁም የሃገር ፍቅር ስሜት ለአላማው በመታመን ወደ አዲሱ ዘመን ተሻግሯል ።



በግዳጅ ውስጥ ሆኖ ምንጊዜም ለላቀ አፈፃፀም የሚዘጋጀው ዕዛችን አመራሩን በየደረጃው አሰልጥኖ በማብቃትና ጠንካራ የመሪነት ክህሎት እንዲላበስ በማድረግ ተዋጊ ኃይላችን በየመሳሪያ ምድቡ እንዲሰለጥንና በታጠቀው መሳሪያ ላይ የላቀ እውቀት እንዲጨብጥ ተደርጓል፡ ፡ ስታፉ ክፍላችንም በየስራ ዘርፉ ሰልጥኖ በመብቃት በተልዕኮው ላይ ግልፅ ግንዛቤ እንዲይዝና የአገልጋይነት መንፈስ እንዲኖረው በማድረጉ ረገድ በበጀት ዓመቱ በተግባር ተመዝኖ የተረጋገጠ ውጤታማ ስራ ተሰርቷል ።

ዕዙ በተሰማራበት የግዳጅ ቀጠና በችግኝ ተከላ በእርከን ስራ በመንገድ ጥገና እና በተለያዩ የልማት ስራዎች ላይ ከህዝብ ጋር እኩል ተሳትፎ በማድረግ ሰላምን ከማስጠበቅ ባሻገር ለሃገር እድገት በሚደረገው ርብርብ ውስጥ የዜግነት ድርሻውን በንቃት ተወጥቷል ።

በቀጣናችን ያሉ የፀጥታ ሃይሎችን የማጠናከርና የመደገፍ ስራዎችን አጠናክረን በመስራት ህዝባችን ወደ ሰላማዊ ኑሮው እንዲመለስ ስኬታማ ተግባራትን ማከናወን ችለናል ።

ዕዛችን በ2017 በጀት ዓመት የስራ አፈፃፀሙ ላይ ጥልቅ ምልከታ አድርጎ ፤ በ2018 አዲስ ዓመት ከፍተኛ የስራ ተነሳሽነትን ፈጥሮ ለላቀ ድል ወደ ፊት ለመስፈንጠር ከምንጊዜውም በላይ ራሱን አዘጋጅቷል ።

ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለሀገር መከላከያ ሠራዊት አመራሮችና አባላት እንዲሁም ሲቪል ሰራተኞች ለ2018 ዓ.ም እንኳን በሠላም አደረሳችሁ እያልኩ አዲሱ አመት የሠላም የልማት የጤና እንዲሆንልን እመኛለሁ፡ ፡ መልካም አዲስ ዓመት ።

# ሌተናል ጀኔራል ሰለሞን ኢተፋ የደቡብ ዕዝ አዛዥ መልዕክት

ደቡብ ዕዝ በተጠናቀቀው 2017 አመት የተሰጠውን ተልዕኮ በስኬት ያከናወነበት አመት ነው። በግዳጅ ቀጠናው የሚንቀሳቀሱትን የታጠቁ ፀረ-ሰላም ኃይሎች በመደምሰስ የግዳጅ ቀጣናውን ሰላም በማረጋገጥ ዜጎች የዕለት ከዕለት ስራቸውን ያለ ስጋት እንዲከውኑ፣ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ፣ ማህበረሰቡ ተንቀሳቅሶ እንዲሰራ አድርጓል። ከመስተዳድር፣ ከፀጥታ አካላትና ከህዝቡ ጋር በጋራ በተሰራው ህግ የማስከበር ስራ በርካታ የታጠቁ ፀረ-ሰላም ኃይሎች እንደ ቡድንም ሆነ በተናጠል ከነ-ትጥቃቸው እጃቸውን በመስጠት ሠላማዊ መንገድ እንዲከተሉ ማድረግ ተችሏል። የቀረበላቸውን የሠላም አማራጭ ባልተቀበሉ የጥፋት ኃይሎች ላይ ደግሞ የማያዳግም እርምጃ በመውሰድ ዕዙ ተልዕኮውን በጀግንነት የፈፀመበት አመት ነው፡ ፡ ደቡብ ዕዝ ሶስት የጎረቤት ሃገራትን የሚያዋስኑ ቀጣናዎችን ደህንነት በአስተማማኝ ብቃት ከመጠበቅ ባሻገር ሌሎች ሃገራዊ እና ቀጣናዊ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ በማስገባት የሚሰጠውን ተልዕኮ በአጭር ጊዜ በድል ለመወጣት በሚያስችል አስተማማኝ ወታደራዊ የዝግጁነት ደረጃ ላይ ይገኛል። አዲሱ 2018 ዓመት የሰላም፣ የጤና የፍቅር እንዲሆን እየተመኘሁ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ ለመከላከያ ሠራዊት አባላትና ቤተሰቦች እንዲሁም ለተቋሙ ሲቪል ሰራተኞች እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሳችሁ እላለሁ።




# ሌተናል ጄኔራል መሀመድ ተሰማ የምስራቅ ዕዝ አዛዥ መልዕክት




የምስራቅ ዕዝ በ2017 በጀት ዓመት በምስራቁ የሀገራችን ክፍል እየሰራ ካለው የፀጥታ ስራ ባሻገር በተለያዩ አካባቢዎች ያጋጠሙ የውስጥ የፀጥታ ችግሮችን ለማስተካከል ውጤታማ የህግ ማስከበር ስራዎችን ሰርቷል።

የአማራ ክልልን እና ኢትዮጵያን ከውድመት በመታደግ የማድረግ አቅማችንን ያሳደግንበት ዓመት ነበር ማለት ይቻላል። ሠራዊታችን ህገ-መንግስታዊ ተልዕኮውን በጥሩ ውጤት እየተወጣና የህዝቡን ሰላምና የሀገሩን ህልውና እያስጠበቀ ይገኛል። ያስመዘገብነውን ድል ለማስቀጠል እንደ ዕዝ ዕቅድ አውጥተን እየሰራን እንገኛለን።

በተጨማሪም የማድረግ አቅማችንን ይበልጥ ለማሳደግ በርካታ የዝግጁነት ስራዎችን የሰራንበት ዓመትም ነው። አሁን ላይ የተገኘው ውጤት የተመዘገበውም ስለ ሀገራቸው ህልውና ሲሉ መስዋዕትነት በከፈሉ ጀግኖች ሰማዕታት ውድ ዋጋ ጭምር ነው።

በቀጣይም የጀግኖች ሰማዕታቱን አደራ በማስቀጠል ለሀገራችን ሰላም ስጋት የሆኑ የውጭ ጠላቶችን ትንኮሳ ማክሸፍ የሚያስችለንን ዝግጁነት በሚገባ ማጠናከር ይኖርብናል። ሀገራችንን ከየትኛውም ስጋት የምንጠብቅበትን ቁርጠኝነት ከመቼውም ጊዜ በላይ ልንታጠቅ ይገባናል። በ2018 አዲስ ዓመት የጀመርናቸውን ትልልቅ ድሎች በማስቀጠል ውጤታማ ዓመት እንደምናሳልፍም እምነቴ ነው።

ለመላው ህዝባችንና ሠራዊታችን አዲሱ ዓመት የሰላም የመተሳሰብ የአንድነትና የስኬት ዘመን እንዲሆን ምኞቴ ነው። ክብርና ሞገስ ለጀግኖች ሰማዕታት!!

# ሌተናል ጄኔራል ሹማ አብደታ የልዩ ዘመቻዎች ዕዝ አዛዥ መልዕክት



የልዩ ዘመቻዎች ዕዝ በ2017 ዓ/ም በጀት አመት በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ፣ ጎንደር፣ ጎጃምና ወሎ ዞኖች የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ ግዳጅን ሲወጣ ቆይቷል። ሁሉም ክፍለ-ጦሮቻችን በዚህ ተልዕኮ ላይ ቆይተዋል።

በተልዕኳቸውም የህዝብን የስልጣን ሉአላዊነት በኃይል በመደፍጠጥ የራሱን ፍላጎት ለማሳካት የተነሳውን የባዕዳ ተልዕኮ ተሸካሚና ተላላኪ ፅንፈኛ ኃይል ላይ ተገቢውን እርምጃ ሲወስዱ ቆይተዋል። በሰራነው የህግ የበላይነትን የማስፈን እና የህዝቦችን የስልጣን ሉአላዊነት የማረጋገጥ ተግባር ከፍተኛ ውጤት አስመዝግበን በተሰማራንበት ቀጠና ሁሉ አንጻራዊ ሰላምን ማስፈን ችለናል።

በተለይ በሰሜን ሸዋ ዞን ከአካባቢዉ ማህበረሰብ፣ የሀገር ሽማግሌዎችና ከሃይማኖት አባቶች ጋር በመተባበር ውጤታማ ስራዎች ተሰርተዋል። ሠራዊታችን በፍፁም ፅናት እና ጀግንነት ዘረፋና ግድያን እየፈፀመ በህዝብ ላይ ካልነገስኩ የሚለውን ኃይል በገባበት ገብቶ በመደምሰስ የህዝቡን ሰላም መልሷል።

ፅንፈኛው ኃይል ለአርሶ-አደሮች መድረስ የሚገባቸውን የግብርና ግብዓቶች እና ለህዝብ የሚቀርቡትን የፍጆታ እቃዎች ጭምር ይዘርፋል። በዚህም ሠራዊታችን የአፈር ማዳበሪያዎችን አጅቦ ለአርሶ አደሩ እንዲከፋፈል በማድረግ ለግብርና ስራው የበኩሉን አስተዋፅኦ አበርክቷል።

በተጨማሪም ዕዛችን ራስን በምግብ ለመቻል በርካታ ሄክታር መሬቶችን በማረስ የቦሎቄና የበቆሎ ምርጥ ዘር በማባዛት ለግብርና ሚኒስቴር በማቅረብ በሀገራዊ ልማት ውስጥ የበኩሉን ሚና ከመወጣቱም በላይ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችን በማምረት፣ ከብቶችን በማደለብና ዶሮዎችን በማርባት የሠራዊቱንና የሠራዊቱን ቤተሰቦች ኑሮ እየደገፈ ነው።

በአቅም ግንባታው ረገድ መሰረታዊ ኮማንዶዎችን፣ አየር ወለድና የልዩ ኃይል ፀረ-ሽብር አባላትን በብዛትና በጥራት በማሰልጠን የክፍሉን አቅም የማጎልበት ስራዎች ተሠርተዋል። የአመራሮችን፣ የአሰልጣኞችን፣ የሙያተኞችን እና የስታፍ አባላትን ብቃት የማሳደግ ተግባራትንም አከናውነናል።

በ2018 ዓ/ም በጀት አመትም የታዩ ክፍተቶችን በማረምና ጠንካራ ጎኖቻችንን በማጎልበት በአዲሱ ዓመትም የህዝባችንን ሰላም በዘላቂነት ለማረጋገጥ እንተጋለን። ለመላው የሀገር መከላከያ ሠራዊት እንኳን ለ2018 አዲሱ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ አደረሰን እላለሁ።

# ብ/ጄኔራል ተስፋዬ ረጋሳ የሪፐብሊኩ ጥበቃ ኃይል አዛዥ መልዕክት

የሪፐብሊኩ ጥበቃ ኃይል ባሳለፍነው 2017 ዓ/ም በርካታ ውጤታማ ስራዎችን በስኬት አከናውኗል። ክፍሉ ተልዕኮውን ለማሳካት እቅድ አውጥቶ ፀጥታ የማስከበር ስራዎችን ሰርቷል። በተጨማሪም በሀገራችን የተከናወኑ አለም አቀፋዊ ስብሰባዎች ሰላማዊ ሆነው እንዲጠናቀቁ ከሌሎች የፀጥታ አካላት ጋር ቅንጇት በመፍጠር አስተማማኝ ጥበቃ አድርጓል። ዘመናዊ ሠራዊት የመገንባት ሂደቱ አካል የሆኑ ለክፍለጦር እና ሻለቃ አመራሮች እንዲሁም ሰልጥኖና አሰልጣኞች በሀገር ውስጥና በውጭ ሃገር ስልጠና እንዲውስዱ ተደርጓል። ዘመናዊ የቪ.አይ.ፒ ጥበቃ እና እጀባ ስራ የሚሰሩ ከውጭ ሀገር በመጡ አሰልጣኞች አሰልጥነናል። በተጨማሪም የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና በሀገር ውስጥ ከቲም መሪ እስከ ሻለቃ አመራር እና የስታፍ ሞያተኞች በማሰልጠን የዘሬና የነገ ተተኪ አመራሮችን ማፍራት ላይ ትኩረት ተደርጎ የተሰራበት አመት ነበር። አዲሱ 2018 ዓመትም የተጠናቀቀውን አመት ስኬታችንን በተሻለ ውጤት የምመናስቀጥልበት ዓመት እንዲሆን ከወዲሁ ዝግጅቶች ተደርገው ሥራዎች እየተሰሩ ነው። አዲሱ ዓመት የሀገራችንን ሰላም ለማወክ የሚሰሩ ፀረ-ሰላም ኃይሎች ሙሉ ለሙሉ የምናፀዳበት፤ የሀገራችንን ሰላም የተሟላ ለማድረግ የምንሰራበት፣ እንደ ተቋም ስኬት የምናስመዘግብበት እንዲሆን እየተመኘሁ ለሪፐብሊኩ ጥበቃ ኃይል አመራርና የሠራዊት፣ አባላት ለመላው መከላከያ ሰራዊት አባላት እና ለጥምር የፀጥታ ኃይሎች እንኳን ለ2018 ዓ/ም በሰላም አደርሳችሁ፤ መልካም አዲስ ዓመት ለማለት እወዳለሁ።



# ሌተናል ጄኔራል ብርሃኑ በቀለ የሰሜን ምዕራብ ዕዝ አዛዥ መልዕክት

የድንበር አካባቢ ሠላምና ፀጥታን ማረጋገጥ፣ ህገ-ወጥ የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴዎችን መቆጣጠር፣ የአማራ ክልልን የብጥብጥና የትርምስ ቀጣና ለማድረግ የሚፍጨረጨሩ ፀረ-ሰላም ኃይሎች የሚፈጥሩትን በመሳሪያ የተደገፈ እንቅስቃሴ አደብ ማስገዛት ለሰሜን ምዕራብ ዕዝ በ2017 ዓ.ም ከተቋሙ ከተሰጡት ተልዕኮዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ዕዙም ይህን ተልዕኮውን ተቀብሎ ጠንካራ ስምሪቶችን በማድረግ የህይወትና የአካል መስዕዋትነት በመክፈል ጭምር ውጤታማ አድርጓል። ዕዙ በኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋሳቢነት የባንዳነት ተልዕኮ ተቀብለው ሀገር የማፍረስ ተግባር ላይ የተሰማሩ ተላላኪዎችን ተግባር የማክሸፍና የሀገራችንን ሉዓላዊነት በዘላቂነት የማስከበር ስራ በስኬት ካከናወናቸው ተልዕኮዎቹ ግንባር ቀደሙ ነው። በዚህም በአማራ ክልል ሊደርስ ይችል የነበረውን ቀውስ ከመቀልበስ ባሻገር ክልሉን ከመፍረስ የታደገ ዕዝ ነው። ሠራዊታችን ህዝባዊ ባህሪውን ጠብቆ ፅንፈኛውን ከህዝብ በመነጠል በወሰዳቸው ጥንቃቄ የተሞላባቸው እርምጃዎች በአሁኑ ወቅት በአማራ ክልል አንፃራዊ ሠላም ማምጣት ተችሏል። የልማት ስራዎችም በመከናወን ላይ ይገኛሉ። የክልሉን ሠላም በፅኑ መሠረት ላይ ለመገንባትም ህብረተሰቡን የማወያየት፣ የፀጥታ መዋቅሩን አቅም የመገንባትና የማጠናከር ብሎም የአካባቢውን ሠላም በራሱ እንዲጠብቅ የማስቻል ስራ በሰፊው ተሰርቷል።

ዕዙ የቀጣናውን ሰላምና ደህንነት እያረጋገጠ ራሱን ለቀጣይ ግዳጅና ተልዕኮ ከማዘጋጀት አንፃርም ውጤታማ ተግባራትን አከናውኗል። ይህም ሠራዊቱ በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆኖ መዋጋት፣ መሰልጠንና መዘጋጀት እንደሚችልና በአንድ ጊዜ በርካታ ግዳጆችን መወጣት የሚያስችል አቅም መፍጠሩን ያሳያል። ዕዙ የስልታዊ አመራሩን ብቃት ማሳደግ እንደ ዋና ስራ ወስዶ ለአመራሩና ለስታፍ ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች አጫጭር የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠት የሠራዊታችንን አካላዊ፣ ስነ-ልቦናዊና ሙያዊ ብቃት የማጎልበት ስኬታማ ስራዎችንም አከናውኗል። ከዚህ በተጨማሪም



የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርንም ትኩረት ሰጥቶ ተግብሯል። ዕዙ በቀጣይ የነበሩ ጥንካሬዎቹን ጠብቆ የሚሰጡትን ግዳጆች በአስተማማኝ ለመወጣት ዝግጁነቱንና ጀግንነቱን አጠናክሮ በተለይ በአማራ ክልል የተገኘውን አንፃራዊ ሠላም በዘላቂነት ለማረጋገጥ ዘራፊው ቡድን የክልሉ ስጋት ወደ ማይሆንበት፣ ክልሉ በግጭቱ ምክንያት የባከኑበትን የልማት ጊዜያት የሚያካክስበት እንዲሆን ይሰራል። በዚህ አጋጣሚ እንደ ዕዝ ለተወጣናቸው ግዳጆች ሁሉ የአማራ ክልል ህዝብና መንግስት እንዲሁም የፀጥታ አካላት ለተልዕኳችን መሳካት ጉልህ አስተዋፅኦ የነበራቸው ሲሆን በቀጣይም ይህንን ድጋፍና ትብብር አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪዬን አቀርባለሁ። 2018 አዲስ ዓመት አገራችን ሠላሟ የተረጋገጠ፣ የዕድገትና የብልፅግና ጉዞዋ የተሳካ እንዲሆን እየተመኘሁ በድጋሚ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ ለመላው የመከላከያ ሠራዊት አባላት፣ ለሰሜን ምዕራብ ዕዝ የሠራዊት አባላትና ሲቪል ሰራተኞች እንኳን አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ አመሰግናለሁ።

# ሌተናል ጄነራል አሰፋ ቸኮል የሰሜን ምስራቅ ዕዝ አዛዥ መልዕክት



በሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ ለምትኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣ በሀገራችን አራቱም አቅጣጫ ሀገራዊ ግዳጃችሁን በመወጣት ለኢትዮጵያ እና ህዝቦቿ ሰላም ስትሉ ሁለንተናዊ መስዋዕትነት በመክፈል ላይ ለምትገኙ የጀግናው መከላከያ ሠራዊታችን አባላት እና የሠራዊቱ ቤተሰቦች እንዲሁም በአለም አቀፍ ሰላም ማስከበር ተልዕኮ ላይ ተሰማርታችሁ ለምትገኙ የሠራዊታችን አባላት እና ሲቪል ሰራተኞች፣ ለመላው የሰሜን ምስራቅ ዕዝ የሰራዊት አባላት እና አመራሮች በሙሉ:: ከሁሉ አስቀድሜ እንኳን ለ2018 ዓ/ም አዲስ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ፣ አደረሰን እያልኩ አዲሱ አመት የሰላም፣ የእድገት እና የብልፅግና ዘመን እንዲሆንልን እመኛለሁ።

በመቀጠል ሁላችንም እንደምናውቀው ሠራዊታችን በሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ የተሰጡትን ግዳጆች በታላቅ ጀግንነት እና ፅናት በመፈፀም ጠላቶቻችንን እያሳፈረና ሴራቸውን እያመከነ ኢትዮጵያን እና ህዝቦቿን እያኮራ የሚገኝ የድል ሠራዊት ነው።

ተቋማችን መከላከያ ላለፉት ሰባት ዓመታት ባካሄደው ተቋማዊ ሪፎርም ሠራዊታችን ከማንኛውም ውግንና በፀዳ መልኩ ዘመናዊ ሠራዊት ሆኖ ተገንብቷል። በመገንባት ላይም ነው። በተሰማራበት ተልዕኮ ሁሉ ግዳጁን ሲፈፅም በህዝባዊ ባህሪው እና በሪፎርሙ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ ነው።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ አካል የሆነው የሰሜን ምስራቅ ዕዝም የተቋሙን ሪፎርም ለመፈፀም ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወነ መጥቷል። አሁንም ሂደቱ ተጠናቅሮ የቀጠለበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን። እንደ ዕዝ ህዝብ፣ መንግስት እና መከላከያ የሰጡንን ግዳጆች በድል እንድንወጣ ተቋማዊ ሪፎርሙ ከፍተኛ አቅም ሆኖናል።

በዚህ መሰረት የዕዛችን የሠራዊት ክፍሎች በተሰማሩባቸው የግዳጅ ቀጣናዎች ሁሉ ግዳጆቻቸውን በሚገባ በመፈፀም አኩሪ ታሪክ እያስመዘገቡ ይገኛሉ።

ዕዛችን በፅንፈኛው ላይ በወሰዳቸው ተከታታይ እርምጃዎች ጠላት ላይ ከፍትኛ ሰብዓዊ እና ቁሳዊ ኪሳራ ማድረስ ተችሏል። ፅንፈኛው ከጊዜ ወደ ጊዜ አቅሙ እየተዳከመ የመጣ ሲሆን እርስ በእርሱ የሚዋጋበትና ወደ ተራ ሽፍትነት ተግባር ለመሰማራት ተገዷል።

አሁን ላይ በየመንደሩ እየተሹለኮሎኩ ሰላም በማደፍረስ ተግባር ላይ የተሰማሩ ፅንፈኞችን ተከታትሎ በአጭር ጊዜ ውስጥ በመደምሰስ ወደ ዋና ሀገራዊ ግዳጃችን ለመመለስ በቀጣዩ ዓመት በትኩረት እንሰራለን። በአዲሱ ዓምት በግዳጅ ቀጣናችን የሚገኙ ፅንፈኞችን በማጥፋት ህዝባችን የሰላም አየር እንዲተነፍስ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ የሚከፈለውን መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ነው።

በሌላ በኩል ከዋና ግዳጃችን ጎን ለጎን የሠራዊታችንን ሁለንተናዊ አቅም ለማሳደግ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወንን መጥተናል። የዕዛችን የሠራዊት ክፍሎች የስነ- ልቦና፣ የወታደራዊ ንድፈ-ሃሳብ እና የተግባራዊ ውጊያ አቅማቸውን በማላቅ በማንኛውም ግዳጅ እና ሁኔታ የላቀ ውጤት ማስመዝገብ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል።

ዕዛችን በግዳጅ ቀጣናው ከሚገኙ የአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ተባብሮ እና ተከባብሮ በመስራት በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነትንና አክብሮትን አትርፏል። ስለሆነም ማህበረሰቡ ጠላትን አምርሮ በመጥላት፣ በማጋለጥ እና በተግባር በመታገል ደጀንነቱን እያረጋገጠ ይገኛል። በአገራችን የሚካሄዱ የልማት ስራዎች እንዳይደናቀፉ ሰላምን የማፅናት እና ፀጥታ የማስከበር ስራዎቻችንን በትጋት በመፈፀም በቀጣናችን ዘላቂ ሰላም ለማረጋገጥ የምናደርገው ጥረት ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን በድጋሜ ላረጋግጥ እወዳለሁ። አመሰግናለሁ::

# ሜጀር ጄኔራል ብርሀኑ ጥላሁን የ6ኛ ዕዝ አዛዥ መልዕክት

ከሁሉ አስቀድሜ ለመላ ኢትዮጵያዊያን፣ ለተቋማችን መከላከያ ዓመራሮችና አባላት፣ ለዕዛችን አመራሮችና አባላት፣ እንዲሁም ሲቪል ሰራተኞች እንኳን ለ2018 ዓ.ም አዲስ ዓመት አደረሳችሁ ማለት እወዳለሁ:: ዕዛችን በ2017 ዓ/ም ተልዕኮውን የተዋጣው በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች ውስጥ ነው:: በነዚህ ክልሎች ደግሞ መሳሪያ የታጠቁ ፀረ ሰላም ሃይሎች በስፋት እንቅስቃሴ የሚያደርጉባቸው አካባቢዎች አሉ:: እነዚህ አካባቢዎችን ከታጠቁ ቡድኖች ነፃ ማድረግ ደግሞ የዕዙ ዋና ተልዕኮና ግዳጅ ነበር:: ይህንን ተልዕኮ መነሻ በማድረግም ዕዙ ሰፋፊ ስምሪቶችን አድርጓል::

ዕዙ ወደ ጠቀስናቸው አካባቢዎች ተልዕኮ ተቀብሎ ሲሰማራ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች በፀረ ሰላም ኃይሎች ተይዘውና የመንግስት መዋቅር እንደ ልብ የማይሰሩበት፣ መንገዶች የተዘጋጉበት፣ የማህበረሰቡ እንቅስቃሴ ተገድቦ ለከፋ ችግር ተዳርጎ የነበረበት ሁኔታ ነበር:: ይህንን ለማስተካከል ከፍተኛ ስራ ተሰርቷል:: በተሰራው ስራም በፀረ-ሳላም ኃይሎች ተይዘው የነበሩ በርካታ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ነፃ ሆነዋል:: የዕዙ ተልዕኮ ግብም ይህ ነው:: የጠላት ዋና ዋና የስበት ማዕከሎች ተመተዋል:: ማህበረሰቡም እረፍት አግኝቷል:: በርካታ የፀረ-ሰላም ቡድኖች አመራርና አባላት እጅ ሰጥተዋል:: መሳሪያ አስረክበዋል:: በዚህም ህዝብ የሚፈልገውን ሰላም አንፃራዊ ማድረግ ተችሏል:: በአጠቃላይ ስድስተኛ ዕዝ ባሳለፍነው 2017 ዓ.ም ውጤታማ የግዳጅ አፈፃፀም ያስመዘገበበት ዓመት ነው:: በ2018 ዓ/ም አዲስ ዓመትም በግዳጅ ቀጣናው የቀሩ የጠላት ርዝራዦችን በመጨረስ አካባቢውን ሙሉ ለሙሉ ሰላም ማድረግ ሲሆን ለዚህ የሚሆን ዕቅድ ተዘጋጅቶም ወደ ትግበራ ተገብቷል::

ጠላት በርካታ ኃይሉ የተደመሰሰና እጅ የሰጠ ቢሆንም አሁንም በትንሽ ኃይል ሠራዊቱ ባልደረሰባቸው በረሀማ ቦታዎች ላይ በሽፍታ መልክ የሚንቀሳቀሱ ሲሆን በቀጣይ አመት ይህንን ጨርሰን ሰላሙን ሙሉ በማድረግ ለክልሎች የምናስረክብበት እንደሚሆን ሙሉ እምነት አለኝ:: አዲሱ አመት የኢትዮጵያ ሰላምና እድገት የሚረጋገጥበት እንዲሆንም መልካም ምኞቴ ነው:: አመሰግናለሁ::





# ኮሞዶር ተገኝ ለታ የኢትዮጵያ ባህር ኃይል ምክትል አዛዥ ለውጊያ ድጋፍ አገልግሎት መልዕክት

ተቋሙ ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ባህር ኃይልን እንደገና የማደራጀት ስራ እየተሰራ ነው። በዚህ ሂደት በ2017 ዓ.ም በርካታ የአቅም ግንባታ ስራዎች ተሰርተዋል። ክፍሉን በሰው ኃይልና በማቴሪያል አቅሙን ለመገንባት ስኬታማ ስራዎች ተከናውነዋል። ኢትዮጵያ ዝነኛ ባህር ኃይል ነበራት። ይህን የፈረሰውን ክፍል እንደገና ማደራጀት ደግሞ ተቋሙን ሙሉ ከማድረጉም በላይ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ፣ ፓለቲካዊና ማህበራዊ ጥቅም ከፍተኛ ከፍተኛ ድርሻ አለው። በእርግጥ ክፍሉን እንደገና ለማደራጀት ትልቅ ሀብትና ጊዜ የሚጠይቅ ቢሆንም በተጠናቀቀው 2017 ዓ.ም ወሳኝ ስራዎች ተከናውነዋል። የባህር ሃይል ጠቅላይ መምሪያን ጨምሮ የባህረኞች ማሰልጠኛ ማዕከል፤ በቀጣይነት የሰው ሃይል አቅም መገንባት የሚያስችሉ የትምህርትና ስልጠና ተቋሞች ተገንብተው ወደ ተግባር እንዲሸጋገሩ የተቀናጀ ጥረት በማድረግ የተግባር ሥራዎች ተሠርቷል። በተጨማሪም ከሌሎች የፀጥታ አካላት ጋር በመቀናጀት የሀገራችንን ፀጥታ የማስከበር ስራ የሰራን ሲሆን የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ላይም ከማህበረሰቡ፣ ከመከላከያ ክብር አባላቶች ጋር በመሆን አከናውነናል። ለመላ የኢትዮጵያ ህዝብ፤ ለመላ መከላከያ ሠራዊታችንና ለባህር ኃይል አባላትና ሲቪል ሰራተኞች በሙሉ እንኳን ለ2018 ዓ/ም አዲሱ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ ማለት እወዳለሁ።

# ወታደራዊ ዲፕሎማሲያችን

በአብርሃም ዘርጋው (ፕ/ኦ)
የጋዜጣው ሪፓርተር

ባሰፋት የታሪክ ምዕራፎች የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የሀገር ህልውና ወሳኝ ምሰሶ ሆኖ ቆይቷል። ይህ ሠራዊት፣ ዛሬም በአዲስ ምዕራፍ በአዲስ ወታደራዊ ስትራቴጂ ክንዱን በዲፕሎማሲያዊ ብልሃት እና ጥበብ እየደገፈ ይገኛል። ከጦር ሜዳ ጀግንነት ባሻገርም፣ የሀገርን ሉዓላዊነት፣ ክብርና ጥቅም የሚያስጠብቅ "ዲፕሎማሲያዊ ወታደራዊ ክንፍም" ተገንብቷል። በሜጀር ጄኔራል ተሾመ ገመቹ ይመራል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ሠራዊት የውጭ ግንኙነት እና ወታደራዊ ትብብር ዋና ዳይሬክቶሬት በዓመቱ የሰራቸው ዋና ዋና ስራዎችን፤ በዚህ መሰናዶ እንቃኛለን። ከጄኔራሉ ጋር ባደረግነው ቆይታ፣ የዚህ አዲስ ክንፍ ተልዕኮ፣ ስኬቶች እና የወደፊት ራዕይ፣ የዲፕሎማሲው ኃይል ከጥይት በላይ ካለው ፋይዳ አንፃር በጥልቀት ተብራርቷል።


ፎቶ፡-ከማህደር

ሜጀር ጄኔራል ተሾመ ገመቹ
የመከላከያ የውጭ ግንኙነት እና ወታደራዊ ትብብር ዋና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

## የዋና ዳይሬክቶሬቱ ዓላማ

ጠንካራና ውጤታማ ወታደራዊ ዲፕሎማሲን በሚገባ ተግባራዊ በማድረግ ከዘርፉ ከሚገኙት ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች የተቋማችንን ዋነኛ ተልዕኮ መደገፍ፣ ተቋማዊ በጎ ገፅታን ማስረፅ እንዲሁም ቀጣይነት ያለው የአቅም ግንባታ ላይ የበኩሉን ድርሻ ማበርከት።

## የዋና ዳይሬክቶሬቱ የትኩረት መስኮች ወይም ማጠንጠኛዎች

- የፓለቲካ ድጋፍ ማግኘት
- የአምስተኛ ትውልድ አቅም ግንባታን የሚወስኑ ስልጠናዎችን ማግኘት
- የተቋማችንን በጎ ገፅታና የሰራዊታችንን ክብርና ዝናን በውጭው ዓለም ማስረፅ
- የሎጀስቲክስና ወታዳራዊ ቁሳቁሶች ድጋፍ እንድናገኝ ማድረግ
- የተለያዩ የገንዘብ ድጋፎች እንድናገኝ ማድረግ
- የክፍሉን የመፈፀም አቅሞችን መፍጠር ላይ ያተኮረ ስራዎችን መስራት
- ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽና ወቅቱን የጠበቀ አገልግሎት በመስጠት መልካም ገፅታን ማስረፅና ተገልጋዩን ማርካት
- የተቋሙን አመራሮች የውሳኔ ሰጪነትን፣ መተጣጠፍን ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ ስትራቴጂክ መረጃዎች ከውጭው ዓለም ወዳጆቻችን ማግኘት

## የዋና ዳይሬክቶሬቱ ተልዕኮ

የሀገሪቱን የውጭ ግንኙነት ፓሊሲ መሠረት በማድረግ ተቋሙን ከውጭ ሀገራትና ተቋማት ጋር ማገናኘት፤ የወታደራዊ ዲፕሎማሲ፤ የአቅም ግንባታና የገፅታ ግንባታ ተግባራትን ማከናወን ፤የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የስልጠና ዕድሎችን ማምጣት፣ ውሎችና ስምምነቶች ብሔራዊ ፍላጎትን የሚያረጋግጡና የተማከሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ ለውሳኔ ማቅረብና በተጨባጭ መረጃና እውቀት ላይ በመመስረት የጎረቤት ሀገሮች አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ትብብርና ግንኙነትና የፀጥታና ደህንነት ተጨባጭ ሁኔታዎችን በመከታተል ለወታደራዊ ትብብር ግንኙነት የሚያግዙ ስራዎችን ማከናወን።

## ምስጢራዊነት እና ግልጽነት፡ ሚዛኑን የጠበቀ የጥበብ መንገድ

የሀገርን ህልውና በሚያጸና ተቋም ውስጥ ምስጢር መጠበቅ እንደ ዓይን ብሌን ጥብቅ ነው። ሆኖም ግን፣ በዲፕሎማሲው ዓለም ውስጥ ይህ ምስጢራዊነት ከጥበብ ግልጽነት ጋር ሚዛኑን መጠበቅ አለበት። ጄኔራሉ እንዳስረዱት፣ በኢትዮጵያ ለሚገኙ የውጭ ወታደራዊ አታሼዎች ስለ ሀገሪቱ ሰላምና ደህንነት ትክክለኛ መረጃ መስጠት ወሳኝ ነው። "የተዛባ እና የተሳሳተ መረጃ ከልዩ ልዩ የመረጃ ምንጮቻቸው ከሚወስዱ ይልቅ፣ ከራሳችን ተጨባጩን፤ ትክክለኛውን የመሬት ላይ እውነታ ማሳወቅ ሀገራችን ላይ የደበዘዘ እይታ እንዳይኖራቸው ማድረግ ቀዳሚ ተግባራችን ነው" ሲሉ የትክክለኛ መረጃን ዋጋ አስረድተዋል። በዚህ ዘመናዊና በቴክኖሎጂ ጥበብ በተሳሰረና በረቀቀ ዓለም በሩን መዝጋት "በራስ ላይ ሸምቀቆ እንደማጥለቅ ይቆጠራል። ባልተገባ መንገድ እንዲተረጎም በር እንደሚከፍት ጄኔራሉ ገልጸዋል። እንደ ጄኔራሉ አገባብ አስፈላጊ ወታደራዊ መረጃዎች ብቻ ይፋ ማድረግ ግልፀኝነትን ይፈጥራል።

## የወታደራዊ ዲፕሎማሲ ፋይዳ እና የኢትዮጵያ ተስፋ!

ኢትዮጵያ በቀጠናው ያላት የማይናወጥ ተፅዕኖ እና የዓለም ማህበረሰብ የሚጥልባት ታላቅ እምነት፣ ወታደራዊ ዲፕሎማሲን የሀገሪቱ የህልውና ወሳኝ ጉዳይ ያደርገዋል። "ፓለቲካዊ ድጋፍ ለማግኘትም ቢሆን አስፈላጊ ነው" የሚሉት ጄኔራሉ፣ ይህ ድጋፍ በሀገራችን ላይ ሲደርስ የሚችለውን ተፅዕኖ ለመመከት፣ ወዳጆች እንደ እኛ ሆነው እውነታውን በመናገር፣ በዲፕሎማሲው ጎዳና ስለ እኛ እንዲሟገቱ ማድረግ የሚያስችል ጉልበት እንደሆነ ገልጸዋል። በዚህ ዘመን የብሔራዊ ጥቅምን በብቸኝነት ማስጠበቅ አዳጋች በመሆኑ፣ በዲፕሎማሲ አማካኝነት ወዳጆቻችን እንደ እኛ ሆነው እንዲናገሩ ማድረግ የፓለቲካዊ ድጋፍ ቁንጮ ነው።

"በሶማሊያ የኢትዮጵያ ሠራዊት የከፈለው የጀግንነት መስዋዕትነት እና ከዚያ እንዲወጣ የተሸረበው ሴራ የአደባባይ ምስጢር ነው" ይላሉ። ጄኔራሉ እንዳስታወሱት፣ "በዚህ ረገድ መንግስታችን ታላቅ ስራ እንደሰራው ሁሉ፤ መከላከያ በዲፕሎማሲው ስራ በተመረጡ 12 ሀገራት አታሼዎች ላይ ወሳኝ ድጋፍ እንድናገኝ ተሰርቷል። የኢትዮጵያ ሠራዊት በሶማሊያ መቆየት ለሀገሪቱ ብቻ ሳይሆን ለቀጠናው ሰላም ወሳኝ መሆኑን፣ ሌላ ኃይል ተክቶ ለመስራት ፈጽሞ እንደማይችል፣ ስለሆነም በትብብር በመስራትና ወንድማማችነትን በማጠናከር የጋራ ጥቅምን ማረጋገጥ እንደሚቻል ማስረዳት በመቻሉ፡ ሀገራት በማንኛውም ሁኔታ ከኢትዮጵያ ጎን እንዲቆሙ ማድረግ ተችሏል። ይህም የፓለቲካዊ ድጋፍ ጥንካሬ ማሳያ ነው። በዚህ ዓመት ከተሰሩት ትልልቅ ተግባራት አንዱ ይህ ነው!" ሲሉ ጄኔራሉ አብራርተዋል።

## የሠራዊቱን ክብርና ዝና እንዲሁም የተቋሙን በጎ ገፅታ በውጭው አለም ማስረፅ

በሀገር ውስጥም ሆነ በቀጠናው የመከላከያ ሰራዊት ታላላቅ ግዳጆችን ቢወጣም፣ አልፎ አልፎ የሠራዊታችንን መልካም ስም የማጠልሸትና የማጉደፍ ጥረቶች ይደረጋሉ። ጄኔራሉ "ይህ ትክክል አለመሆኑን እና የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በጠንካራ ዲሲፕሊን የሚመራ የወታደራዊ ፕሮፌሽናሊዝም ምሰሶ መሆኑን የሚያጎሉ የዲፕሎማሲ ስራዎች ተሰርተዋል፣ አሁንም እየተሰሩ ነው" ብለዋል። የመከላከያ ሰራዊት ግዳጁን የተወጣባቸው ቦታዎች የውጭ አታሼ ማህበረሰብ ሄዶ እንዲያይ በማድረግ፣ ሠራዊቱ ከተማ እንደማያፈርስ፣ የህዝብን መብት እንደማይነካ፣ እንደማይዘርፍ፣ በህዝብ ላይ ጫና እንደማያደርስ፣ ከዚህ ይልቅ የራሱን ሬሽን ለህዝቡ እንደሚያካፍል፣ ርህሩህ እና ህግን ጠብቆ የሚሰራ ጀግና ሠራዊት መሆኑን በማስገንዘብ የውጭው ዓለም ስለ ሰራዊታችን ትክክለኛ ገፅታ እንዲኖረው ተሰርቷል።

የኢትዮጵያ የጥበብ መንገድ!

ኢትዮጵያ ከሀገራት ጋር የምታደርገው ግንኙነት በሁለት የማይነቃነቁ ምሰሶዎች ላይ የተመሰረተ ነው፤ እነሱም 1ኛ የጋራ ጥቅም፣ 2ኛ በመከባበር ላይ የተመሰረቱ ግንኙነቶች ናቸው። ጄኔራሉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ወታደራዊ የግንኙነት መርህም ይህ መሆኑን እና በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ፈጽሞ እንደማይደራደር በጥሞና አብራርተዋል። ይህ አብይ መርህ ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፓሊሲ በቀጥታ የመነጨ ነው።

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከየትኛውም ጊዜ በላይ በተሻለና በላቀ ጠንካራ ወታደራዊ ቁመና ላይ ትገኛለች። ስለ ትብብርና አብሮ መስራት ሲታሰብ፣ ኢትዮጵያ ልመና ላይ ብቻ የተመሰረተ ትብብር አትፈልግም። "ትብብር ሲደረግ እነሱ ምንድን ነው ወደ ጠረጴዛ የሚያመጡት፤ እኛስ ምንድን ነው የምናቀርበው" በማለት የጋራ ተጠቃሚነት መርህ እንዳለ አስቀምጠዋል። ማንኛውም የትብብር ስራ የብሔራዊ ጥቅምን የማይጎዳ መሆን እንዳለበትም አጽንዖት ሰጥተዋል ጄኔራሉ።

## ትብብር ከፓለቲካዊ ድጋፍ እስከ ቴክኖሎጂ አድማስ!

በመተማመን ላይ የተመሰረተ ትብብር በተለያዩ መንገድ ይገለጻል። ከላይ እንደተገለጸው ፓለቲካዊ ድጋፍ ለማግኘት፣ ወዳጅ ሀገራት ኢትዮጵያ ላይ የሚደርሰውን ተፅዕኖ በመመከት እንዲሟገቱ የዲፕሎማሲ ስራዎች እየተሰሩ ናቸው። ወዳጅ ሀገራት ይህን ሲያደርጉ ደግሞ ኢትዮጵያም በቀጠናው የተሻለ ቁመናና ልምድ ያለው ሠራዊት ያላት በመሆኗ፣ በቀጠናው ሰላምና ደህንነትን ከማስጠበቅ አኳያ የጋራ ስራዎች ይሰራሉ። ከሌሎች የትብብር ዘርፎች መካከል ወታደራዊ ሎጅስቲክስ፣ የአቅም ማሳደግ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራት በዋነኝነት የሚጠቀሱ የግንኙነት መርህዎች ናቸው።


ፎቶ፡-ከማህደር

የተለያዩ ሀገራት አታሼዎች የታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብን በጎበኙበት ወቅት

## ለ5ተኛው ትውልድ ጦርነት የሚመጥን ስልጠና!

የሠራዊቱን የማድረግ አቅም ለማሳደግ ዘመናዊና ተከታታይነት ያለው ስልጠና መስጠት የተቋሙ ዋነኛ የህይወት እስትንፋስ ነው። ዋና ዳይሬክቶሬቱ ለዚህም የተለያዩ በሮችን በማንኳኳት፣ የተለያዩ ስልጠናዎችን ያስገኛል። እነዚህ ሁሉ ተደማምረው የተቋሙን የማድረግ አቅም ወደር የለሽ ከፍታ ላይ ለማድረስ ያለሙ ናቸው። በአሁኑ ወቅት እየተሰጡ ያሉት ስልጠናዎች የ5ተኛውን ትውልድ የጦርነት አቅም የሚያሳድጉና የሚያጎለብቱ፣ በአገራችን የማይሸፈኑ ግን የ5ተኛውን ትውልድ የጦርነት አቅም የሚወስኑ ናቸው። ለወደፊት ሊመጡ የሚችሉ ተግዳሮቶችና ስጋቶችን ለመቀልበስ ታሳቢ ያደረጉ ናቸው። ይህ እጅግ አበረታችና የድል አድራጊነታችን ማሳለጫ መንገድ ነው!

ከዚህም ባሻገር ወደ ውጭ ብቻ ሳይሆን ከወዳጅ ሀገራትም ጭምር ወታደራዊ አባላት እየመጡ ይሰለጥናሉ። የሚሰለጥኑትም ስልጠና ሠራዊታችን ካለው የላቀ ተሞክሮ፣ ብቃት፣ ዲሲፕሊን እና አጠቃላይ አቅም አንጻር ብዙ ጠቃሚ ተሞክሮዎችን እየወሰዱ መሆኑን የሌላው ዓለም ተማሪዎቹ እንደሚገልጹ ጄኔራሉ አስረድተዋል። በአጠቃላይ የተቋሙ ወታደራዊ ኢንዱስትሪዎች ገበያ ለማፈላለግ፣ የሠራዊቱን አቅም ለማሳደግ እና የተጀመረውን የዘመናዊ ሠራዊት ግንባታ ሂደት ለማሳለጥ የተለያዩ የውጭ ሀገራት ስልጠናዎችን ለማስፋት የትብብር ስራዎች ተሰርተዋል፣ አሁንም በስፋት እየተሰሩ ነው!

## የስኬታማው ተልዕኮ ምስጢር፡ የሰው ኃይልና የጋራ ራዕይ!

ለዋና ዳይሬክቶሬቱ ስኬታማ ተልዕኮ ዋነኛ አቅም የሆነው፣ በመጀመሪያ የተሰጠው ግልጽና የማያሻማ ተልዕኮ ነው። ሌላው ደግሞ በውስጡ ያለው የሰው ኃይል ብርቱ ስብስብ መሆኑ ነው። የዋና ዳይሬክቶሬቱ መላው አባላት የጋራ ትኩረት የሚያደርጉባቸውን ነጥቦች ተገንዝበው፤ የየበኩላቸውን ድርሻ በብቃት፣ በውጤታማነት እና በታላቅ የሀገር ፍቅር ስሜት ያከናውናሉ። <<እንዱ የስኬታችን ምስጢር እሱ ነው" ሲሉ ሜ/ጄኔራል ተሾመ የቡድን ስራን ዋጋ አጉልተዋል። የባለድርሻ አካላት ሚናም ቀላል እንዳልነበረና ስራዎችም በተናበበ መንገድ እንደሚከናወኑ ጠቁመዋል። ሌላው የተቋሙ ከፍተኛ ስትራቴጂክ አመራሮች የማይቋረጥ ክትትልና ደጋፊነት ለስኬቱ አይተኬ ሚና እንደተጫወተ እና አመቺ የስራ ከባቢ እንደፈጠረ ገልጸው የሚቆጠሩና የሚያኮሩ ተጨባጭ ውጤቶችም መታየታቸውን አብራርተዋል።

መልካም ምኞት ለኢትዮጵያና ለጀግናው ሠራዊት፡ የመጪው ዘመን ብርሃን!

በመጨረሻም ሜ/ጄኔራል ተሾመ ገመቹ ለኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት፣ ሲቪል ሠራተኞች እና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ መልካም ምኞታቸውን አቅርበዋል። "የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በተሰለፈበት ሁሉ አገርን የሚያኮራ እና በታላቅ የአገር ፍቅር ስሜት፣ በብቃት እና በውጤታማነት ግዳጁን በቀንና በሌሊት እየፈጸመ ያለ ነው። የሃገሩን ብሔራዊ ጥቅም በደሙና በላቡ እያስከበረ ላለው ጀግናው ሠራዊታችን መጭው 2018 ዓ.ም የተሻለ የዘመናዊ ሠራዊት ከፍታ የምንደርስበት የድል ዓመት እንዲሆን እመኛለሁ!" ሲሉ መልካም ምኞታቸውን ገልፀዋል። ጄኔራሉ "ለኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ የልማት፣ የእድገት፣ መተባበር፣ የሰላም፣ የፍቅር፣ አንድነት፣ ለብሄራዊ ጥቅም አንድ መሆንን እመኛለሁ" ብለዋል። እኛም በቆለ ምልልሳችን ባግኘነው መረጃ በጣም ረክተናል። በለውጡም ተስፋ ሰንቀናል። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የዲፕሎማሲው ክንፍ፣ ለሀገር ህልውናና ክብር የማይተካ ኃይል መሆኑን በቆይታችን ተገንዝበናል!።

# የውጊያ ድጋፍ. . .

ከገፅ 5 የዞረ

በማረጋገጥ በርካታ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡ ፡ በዚህም ጥሩ የሚባል ውጤት ተመዝግቧል፡ ፡ ይህ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡ ፡

"በሽታን ከማከም መከላከል ይቀድማል" እንደሚባለው፣ የመከላከያ የጤና ዋና መምሪያ ዋነኛ ትኩረት አድርጎ ከሚሰራቸው ስራዎች መካከል ሠራዊቱ ለበሽታ እንዳይጋለጥ የሚያስችሉ የመከላከል ሥራዎች ናቸው ። የመከላከል ሥራን በማጠናከር ብቃት ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖር ማድረግ ወሳኝ ተግባር ነው ። በሽታን አስቀድሞ የመከላከል ስራ መስራት ችግሩን ሙሉ ለሙሉ ማስወገድ ባይቻልም ለግዳጅ እንቅፋት እንዳይሆን ማድረግ ግን ይቻላል ።

ይህንን ለማሳካት በየደረጃው ላሉ የሠራዊቱ አባላት ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችና ሥልጠናዎች ይሰጣሉ ። በተለይም በውጊያ ቀጠናዎችና በመኖርያ ሠፈር አካባቢዎች ሊከሰቱ የሚችሉ ተላላፊ በሽታዎችንና ሌሎች የጤና እክሎችን አስቀድሞ ለመከላከል የሚያስችሉ ሳይንሳዊ ጥናቶች ይካሄዳሉ ። በነዚህ ጥናቶች ላይ ተመስርቶም አስፈላጊው የቅድመ ጥንቃቄ እርምጃዎች ይወሰዳሉ ። ለምሳሌ፣ የወባ በሽታን ለመከላከል የአካባቢ ጽዳት፣ የአጎበር አጠቃቀምና ሌሎች የመከላከያ ዘዴዎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል ።

የማንኛውም የጤና ሥርዓት ስኬት የሚለካው ብቃት ባላቸውና በሙያቸው በሚተማመኑ ባለሙያዎች ነው ። ስለዚህ ብቃት ያለው ሙያተኛ ማፍራት ለጤና አገልግሎት የጀርባ አጥንት የሆነ ተግባር ነው፡ ፡ የሰው ልጅ የዘራውን ነው የሚያጭደው፡ ፡ ይህንን እውነታ በመገንዘብ መምሪያው ብቃት ያላቸው ባለሙያዎችን ከማፍራት ጀምሮ የሙያ ክህሎታቸውን በየጊዜው እስከማሳደግ ድረስ ሰፊ ሥራዎችን በማከናወን የጥረቱን ፍሬ ያየበትን ሙተኞችን አፍርቷል፡ ፡

ሌላው የሥልጠና ተቋማትን ማጠናከር ነው፡ ፡ ስለዚህ በመከላከያ ሥር የሚገኙ የጤና ኮሌጆችን የማጠናከር ስራዎች ተሰርተዋል፡ ፡ በአሁኑ ወቅት ሦስት የጤና ኮሌጆች በከፍተኛ ደረጃ ሥልጠና እየሰጡ ይገኛሉ ። እነዚህ ኮሌጆች ከጤና ሳይንስ ኮሌጅና ከመከላከያ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመቀናጀት የማድረግ አቅማቸውን እንዲያጠናክሩ እየተደረገ ነው ። ይህ ትስስር የሥልጠና ጥራትን ከማረጋገጡም በላይ ተመራቂዎቹ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል ።

የሥልጠና አሰጣጡ በደረጃ የተከፈለና እርስ በእርሱ የተሳሰረ ነው ። የደረጃ በደረጃ ሥልጠና የሰው ኃይል ልማቱ የተጠናከረ እንዲሆን ያደርጋል ። ለምሳሌ በክፍለ ጦርና በኮር ደረጃ የፕራይመሪ ሙያተኞችን በማሰልጠን፣ የመከላከል አገልግሎቱ ጠንካራ እንዲሆን ይደረጋል ። እነዚህ ባለሙያዎች በግዳጅ ወቅት የሚያጋጥሙ መሰረታዊ የጤና ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል እውቀትና ክህሎት ይኖራቸዋል ። እንዲሁም በግንባር ሆስፒታሎች ደረጃ አራት ወይም የዲፕሎማ ሥልጠና ይሰጣል ። ይህ ሥልጠና ከፕራይመሪ ባለሙያዎች መካከል ብቃት ያላቸውን በመመልመል የሚሰጥ ሲሆን፣ በዚህ መሰረት በ2017 ዓ.ም በርካታ ባለሙያዎች በዲፕሎማ ሰልጥነው ወደ ሠራዊቱ ተቀላቅለዋል ። ሌላው በመካከለኛ ደረጃ በዲግሪ መርሀ ግብር የሚሰለጥኑ ተማሪዎችም አሉ ። እነዚህ ተማሪዎች በደረጃ አራት የሰለጠኑና የተሻለ የሥራ አፈጻጸም ያላቸውን በመምረጥ በቀጥታ ወደ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እንዲገቡ ይደረጋል ። ይህ አካሄድ የጤና አገልግሎት አሰጣጡ በሰው ኃይል ብቃት ላይ እንዲመሰረት ያደርገዋል ።

‹‹የቴሌ-ሄልዝ›› አገልግሎትን በማጠናከር፣ በግንባር ያሉ ታካሚዎች ከቦታቸው ሳይንቀሳቀሱ ከልዩ ባለሙያዎች የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ እየተደረገ ነው። ይህ አገልግሎት ከአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራ ሲሆን፣ የህክምና አገልግሎቱን ይበልጥ ተደራሽና ቀልጣፋ አድርጎታል።

ቀጣይነት ያለው የሙያ ማሻሻያ ከማድረግ አንፃርም ከሀገር ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተጨማሪ፣ ከውጭ ሀገራት አጋሮች ጋር በመተባበር በስኮላርሺፕ የልዩ እና የልዕለ- ልዩ ባለሙያዎችን የማሰልጠን ሥራ ይሰራል ። ይህ ሠራዊቱ ውስብስብ የሆኑ የጤና ችግሮችን በራሱ አቅም ለመፍታት የሚያስችለውን ብቃት እንዲገነባ ያግዘዋል ። በዚህ መሰረትም በ2017 ዓ.ም በውጭ ሀገር ሰልጥነው የተመለሱ ባለሙያዎች ወደ ሥራ ገብተዋል ።

ሌላው የጤና መሠረተ ልማቶችን የመገንባት ስራ ነው፡ ፡ በዚህ መሰረት የጤና መሰረተ ልማቶችን የመገንባትና የማደስ ሥራ በስፋት እየተከናወነ ነው ። በግንባር አካባቢዎች ሆስፒታሎች እየተገነቡ ነው ። የእነዚህ ሆስፒታሎች የግንባታ ሂደት ክትትል እየተደረገበት፣ አስተያየቶችን በመቀበል እንደ ግብዓት በመጠቀም ለህክምና አገልግሎት በሚመጥን መልኩ እየተሰራ ነው ። የጦር ኃይሎች ሆስፒታልን ጨምሮ ነባር ተቋማት ላይ ሰፋፊ የእድሳት ሥራ ተሰርቷል ። ለምሳሌ የአላጌ ማገገሚያ ማዕከል እድሳት ተደርጎለት አካባቢው ውብ እንዲሆን በማድረግ ለአገልግሎት ሆኗል፡ ፤ በተመሳሳይ ምቹ የሥራ አካባቢ ከመፍጠር አኳያ የጎፋ መድኃኒት ግምጃ ቤት አካባቢን በማስዋብ ለሠራተኞች ምቹ የሥራ ከባቢ እንዲሆን ተደርጓል ።

የጤና አገልግሎትን ተደራሽነትን እና ጥራት ለማረጋገጥ የመድኃኒትና የህክምና መሣሪያዎች አቅርቦት ወሳኝ ነው ። ጎንለጎንም ሆስፒታሎች ደረጃውን የጠበቀ የህክምና መሣሪያዎችን የማቅረብ ሥራ ተሰርቷል ። በተቻለ መጠን የግብዓት እጥረትን ለመቅረፍ በየወሩ ተደራሽ እንዲሆን ስራዎች ይሰራሉ፡ ፡

በተጨማሪም ‹‹የቴሌ-ሄልዝ›› አገልግሎትን በማጠናከር፣ በግንባር ያሉ ታካሚዎች ከቦታቸው ሳይንቀሳቀሱ ከልዩ ባለሙያዎች የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ እየተደረገ ነው ። ይህ አገልግሎት ከአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራ ሲሆን፣ የህክምና አገልግሎቱን ይበልጥ ተደራሽና ቀልጣፋ አድርጎታል ።



ፎቶ፦ ከማህደር

ውብ፣ ፅዱ፣ ማራኪ እና ለስራ ምቹ የጥገና ማዕከል

በ2017 የበጀት ዓመት የሠራዊቱን የጤና አገልግሎት በማጠናከር ረገድ በርካታ ስኬቶች ተመዝግበዋል ። የሰው ኃይል በማብቃት፣ የጤና ተቋማትን በማደራጀት፣ የመሠረተ ልማቶችን በማሻሻልና የግብዓት አቅርቦትን በማረጋገጥ የተከናወኑ ተግባራት የሠራዊቱን የውጊያ ዝግጁነት በከፍተኛ ደረጃ ያሳደጉ መሆናቸው መረጃዎች ይነግሩናል፡ ፡

ቀጣይ በ2018 በጀት ዓመትም እነዚህን ስኬቶች በማስቀጠልና በማጠናከር የተሻለ ሥራ ለመስራት ታቅዷል ። ዋነኛ ትኩረት የሚደረገው የመከላከል አቅምን በከፍተኛ ደረጃ ማጠናከር ላይ ነው ። ምክንያቱም መከላከል የሀብት ብክነትን ከመቀነሱም በላይ የሠራዊቱን ጤንነት በመጠበቅ ለተልዕኮው ስኬት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል ።

የመከላከያ የጤና ዋና መምሪያ የሰራቸውና እየሰራቸው የሚገኙ ስራዎች በእጅጉ የሚደነቁ ናቸው፡ ፡ ተቋሙ ያስቀመጠውን የአስር ዓመት እስትራቴጅክ እቅድ፤ የሚመጥን የስራ ሂደት ላይ የሚገኝ ዋና መምሪያ ነው ። ዋና መምሪያው ከለውጡ ማግስት በቴክኖሎጅ፣ በሰው ኃይል፣ በስልጠና ተቋማት እና መሰል ጉዳዮች ላይ በቁርጠንነት ወደ ስራ በመግባት በርካታ ስራዎችን እየሰራም ነው፡ ፡

በተመሳሳይ የመከላከያ ሎጀስቲክስ ዋና መምሪያ በርካታ ስራዎችን በላቀ ውጤት እየፈፀመ የሚገኝ ክፍል ነው ። ክፍሉ በ2017 በጀት ዓመት የሰራቸውን ዘርፈ ብዙ ስራዎች የዋና መምሪያው ስነ ልቦና ግንባታ ቡድን አድርሶናል ። እኛም በጥቂቱ እንደሚከተለው ዳስሰነዋል፡ ፡

የውጊያ አገልግሎት ድጋፍ የሚያረጋግጡ እና የመፈፀም አቅም የሚያጠናክሩ ስራዎችም በበጀት ዓመቱ ሲከወኑ የመጡ ተግባራት ናቸው፡ ፡ የሠራዊታችንን ዝግጁነት ከማረጋገጥ አኳያ የጦር መሳሪያዎች፣ ተተኳሾች፣ ዓባሪ ዕቃዎች፣ ተሸከርካሪዎች እንዲሁም ሌሎች ለሠራዊታችን አስፈላጊ የሆኑ ወታደራዊ ንብረቶች በየጊዜው የማሟላት፣ የማረጋገጥ ስራ ተከናውኗል፡ ፡

በሀገር ውስጥ፣ በዓህጉራዊ እና ዓለማቀፋዊ ግዳጅ ላይ ለሚገኙ የሠራዊታችን ክፍሎች ልዩ ልዩ አቅርቦቶች እና ሁለንተናዊ ድጋፎች በየጊዜው ተደራሽ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ተከታታይነት ያላቸው የውጊያ አገልግሎት ድጋፍ የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል ። የሠራዊታችንን የግዳጅ አፈፃፀም የሚያሳልጡ ወጪ ቆጣቢ እና ውጤታማ የሆነ የስምሪት ስርዓት በመዘርጋት የማጓጓዝ እና የጭነት አገልግሎት ስራው በሁሉም ክፍሎች ተደራሽ እንዲሆን ተደርጓል፡ ፡

የሠራዊታችን ሁለንተናዊ ዝግጁነት የሚያጠናክሩ ተጠጋኝ ንብረቶች ላይ የቅድመ መከላል ስራ በትኩረት ተሰርቷል ። በዚህም በየጊዜው ባጋጠመ ቀላል እና ከባድ ብልሽት ምክንያት እንዲሁም ለረጅም ዓመታት ከአገልግሎት ውጪ ሆነው የቆዩ ተጠጋኝ ንብረቶችን በእድሳት (ሞዲፊኬሽን) ስራዎች በመስራት የኃይል አብዥነት ስራ በመስራት የሠራዊታችንን ዝግጁነት ከፍ ማድረግ ተችሏል፡ ፡

ሁለንተናዊ ዝግጁነትን ለማረጋገጥ እና ግልጋሎታዊ ድጋፍ በተሟላ መንገድ ለመስጠት የተመደበን በጀት ለታለመለት ዓላማ ብቻ እንዲውል በማድረግ ለግዳጅ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ንብረቶች ተለይተው በአዲሱ የመንግስት አሰራር መሰረት ብቻ ግዥ እዲፈፀም ተደርጓዋል፡ ፡

ትኩረት ሰጥቶ በሰራቸው የሠራዊት ግንባታ ስራዎችም ስኬታማ ተግባራትን መከናወን ችሏል ። በተቋሙ በተቀመጠው የግንባታ መርሀ መሰረት የዘመናዊ ሠራዊት ግንባታ ሒደትን በማጠናከር በሥነ-ልቦና ጠንካራ በመሆን ግዳጅን በብቃት መፈጸም የሚያስችሉ ተከታታይነት ያላቸው የግንባታ ስራዎች ተሰርተዋል፡ ፡ የሴቶችን ተሳትፎ ለማረጋጥ ወንድ የሠራዊት አባላትን እና ሲቪል ሰራተኞችን ያሳተፈ ስልጠና እና ውይይቶች በማድረግ ግንዛቤ የሚያሳድጉ ስራዎች ተከናውነዋል፡ ፡

የሠራዊታችን አደረጃጀት በጥናት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን እና የተጀመረውን ሪፎርም ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲከናወን ለማስቻል ከሰው ሀብት ዋና መምሪያ በተሰጠ አቅጣጫ መሰረት በእያንዳንዱ ስራ የሚያስፈልገው የሰው ኃይል እና ሙያተኛ መከናወን የሚገባቸው የስራ መዘርዝሮች የያዘ ዶክመንት የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡ ፡

የንብረት ማከማቻ እና የእድሳት ማዕከላት ውብ፣ ፅዱ፣ ማራኪ እና ለስራ ምቹ የማድረግ ስራ ተሰርተዋል ። ስራው የተሰራው በየደረጃው የሚገኘውን የሎጀስቲክስ ዋና መምሪያ አመራር እና አባላት እንዲሁም ሙያተኛውን በማደራጀት ከመደበኛ ስራ ጎን ለጎን በሳምንት 2 ጊዜ በግንባታው እና በልማት ስራው ተሳትፎ በማድረግ ነው፡ ፡ በተጨማሪም ባለድርሻ አካላት እና የሀገር በቀል ድርጅቶች ድጋፍ አድርገዋል፡ ፡

በሀገራችን የተጀመረውን እራስን በምግብ የመቻል ዘመቻ መነሻ በማድረግ እንደ ተቋም በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ከ300 ሄክታር በላይ በሆነ የእርሻ ማሳ በቢሾፍቱ፣ በዝዋይና መቂ በማዘጋጀት ምርት የመሰብሰብ ስራ ተከናውኗል፡ ፡ በተጨማሪ የሎጀስቲክስ ዋና መምሪያ ማዕከላት ለምግብነት በሚውሉ በቋሚ ፍራፍሬዎች እና በልዩ ልዩ ዛፎች የመሸፈን ስራ ተከናውኗል ።

በኢትዮጵያ የዜጎችን ደህንነት በማረጋገጥ ዘላቂ ሠላምና መረጋጋት እንዲሰፍን ሠራዊታችን እስከ ህይወት መስዋዕትነት እየከፈለ ይገኛል፡ ፡ ይህ ተግባር ተልዕኮውን ከመወጣት ባላፈ ለሀገር፣ ለህዝብ ፍቅር የሚከፈል ዋጋ ጭምር ነው፡ ፡ ተቋሙ ዘመናዊነትን በመላበስ በሁሉም ዘርፎች ጠንካራ አቅም ለመፍጠር በቁርጠኝነት ወደ ስራ መግባቱ ዋል አደር ብሏል፡ ፡ ከላይ በጥቂቱ ለመዳሰስ የሞከርናቸው ክፍሎች የዚህ ማሳያዎች ናቸው እንላለን፡ ፡ ሠላም!

# የ2018 አዲስ ዓመት

ኮራችን በ2017 ዓ/ም የተሰጠውን ተልዕኮ ተቀብሎ በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች በትንሽ ኃይል ብዙ ቦታ በመሸፈን በተዋጣው ግዳጅ አመርቂ ውጤት አስመዝግቧል። በምስራቅና በምዕራብ ጎጃም በርካታ ወረዳና ቀበሌዎችን በመሸፈን ህዝብን ለከፋ ስቃይና እንግልት ሲዳርጉ የነበሩ ኃይሎችን በመደምሰስ የአካባቢውን ሰላም ወደ ነበረበት በመመለስ ተቋርጠው የነበሩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ማድረግ ተችሏል። ህዝቡም ተረጋግቶ የልማት ስራውን እንዲያከናውን ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። በአዲሱ 2018 ዓመትም ቀሪ ፀረ-ሰላም ኃይሎችን ሙሉ ለሙሉ ተከታትሎ በመደምሰስ የህዝብን ዘላቂ ሰላም ለማረጋገጥ በትጋት የምንሰራበት አመት ይሆናል። ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለጀግናው የ6ኛ ዕዝ አመራርና አባላት እንኳን ለ2018ዓ/ም አዲስ ዓመት አደረሳቹ፤ አዲሱ ዓመት የሠላም የጤና የእድገት እንዲሆን መልካም ምኞቴ ነው።



ብርጋዴር ጄኔራል ሰፍያን ሼህ መሀመድ በስድስተኛ ዕዝ ኮር አዛዥ



ብርጋዴር ጄነራል ዘውዱ ሰጥአርጌ የ801ኛ ኮር አዛዥ

ኮሩ ባለፈው 2017 ዓ.ም የተሰጡትን ተልዕኮዎች በውጤታማነት አከናውኗል። የግዳጅ አፈፃፀሙ ስኬታማ ነበር። በግዳጅ ቀጣናው እኩይ ተልዕኮ ይዘው የሚንቀሳቀሱ ፅንፈኞችን ተከታትሎ በመደምሰስ የህብረተሰቡን ሠላም በአንፃራዊነት ማረጋገጥ ችሏል። በቀጣይም የነበረውን ጥንካሬ በማስቀጠል ሠላሙን ሙሉ ለማድረግ ያልተቋረጠ ስራን የሚጠይቅ በመሆኑ የኮሩ አመራርና አባላት በተሟላ ዝግጁነትና ጀግንነት ላይ ይገኛሉ። በ2018 ዓዲስ ዓመት ጥንካሬዎችን በማጎልበት የተሻለ የግዳጅ አፈፃፀም የምናስመዘግብበት ይሆናል። ዓዲሱ ዓመት የሠላም፣ የጤና፣ የአንድነትና የስኬት እንዲሆን መልካም ምኞቴን እየገለፅኩ ለዕዙና ለኮራችን አመራርና አባላት እንንኳን ለ2018 ዓ.ም ዓዲስ ዓመት አደረሳችሁ ማለት እወዳለሁ።

* * *


ኮራችን ባሳለፍነው 2017 ዓ.ም ከዕዙ የተሰጠውን ተልዕኮ ተቀብሎ በላቀ ውጤት በመፈፀም በተሰማራባቸው የግዳጅ ቀጣናዎች ሁሉ የህዝቡን ሰላማዊ ኑሮ ማስተካከል ችሏል። ከዚህ ቀደም በጠላት ቁጥጥር ስር የነበሩ የሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ወረዳዎችና ቀበሌዎችን ከጠላት ተፅዕኖ በማላቀቅ የዞኑ ህዝብ ወደ መደበኛ ሰላማዊ ኑሮው እንዲመለስ አድርገናል። አሁን ላይ በቀጣናው በሰፈነው አንፃራዊ ሰላም ተቋርጠው የነበሩ የልማት እንቅስቃሴዎች በአዲስ መልክ ተጀምረዋል። በቀጣናችን ለተመዘገበው ሰላም የኮራችን የሠራዊት አባላትና አመራሩ ተቀናጅቶ መስራት በጉልህ ተጠቃሽ ነው። አሁን ላይ በግዳጅ ቀጣናችን በቀደሙት ዘመናት ያጋጥሙ የነበሩ የፀጥታ እንከናች ትርጉም ባለው መልኩ መስተካከል ችለዋል። የኮራችን የሠራዊት አመራርና አባላት በቀጣናው ካሉ የሲቪል መስተዳድር አካላት፣ ከአጎራባች ክፍሎችና ከህብረተሰቡ ጋር በቅንጅት መስራት በመቻላቸው በቀጣናው ፈጣን ለውጥ ማምጣት ችለናል። በቀጣዩ 2018 አዲስ አመትም ያስመዘገብናቸውን ውጤቶች አቅበን የቀሩ የጠላት ሴሎችን በመደምሰስ ዘላቂ ሰላም ለማረጋገጥ እንተጋለን። አዲሱን አመት ስንቀበል የኮራችንን አራተኛ አመት የምስረታ ቀን በላቀ ድልና ስኬት ባከበርንበት ማግስት በመሆኑ በቀጣዩ አመትም ለጥሩ ስኬት እንድንተጋ ያደርገናል። ለመላው የመከላከያ ሠራዊታችን፣ ለኮራችን የሠራዊት አመራረና አባላት እንዲሁም ለመላው ህዝባችን አዲሱ ዓመት የሠላም፣ የጤና፣ የትብብር እና የስኬት ዘመን እንዲሆን እየተመኘሁ እንኳን አደረሳችሁ ማለት እወዳለሁ።



ኮሎኔል ረሺድ ኢብራሒም የ401ኛ ቴዎድሮስ ኮር አዛዥ

* * *

ባሳለፍነው 2017 ዓ.ም ምዕራብ ዕዝ የተሰጠውን ግዳጅ 7/24 በመወጣት ተልዕኮውን በአስተማማኝ ፈፅሟል። በዚህ ሂደትም የዕዙ መገናኛና ኢንፎርሜሽን መምሪያ ያልተቋረጠ የሬዲዮ ግንኙነት እንዲኖር በማድረግ የተፈለገው ውጤት እንዲገኝ ሥራውን በሚገባ ሠርቷል። መምሪያው ለዕዙ ግዳጅ መሳካት አስተዋፅዖው ከፍ ያለ ነው። በዓመቱ የሞያተኞችን አቅም ማሳደግ ላይ ትኩረት አድርጎ በመስራት ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀና ያልተቆራረጠ የግንኙነት ትስስር ፈጥሮ ሰርቷል። ክፍሉ በተጠናቀቀው 2017 ዓ.ም የነበረውን ጥንካሬ ጠብቆ በአዲሱ 2018 አመትም የዕዙን ተልዕኮ የሚደግፍና ውጤታማ የማድረግ ኃላፊነቱን በተገቢው ለመዋጣት ዝግጁ ነው። አዲሱ ዓመት የሠላም፣ የጤና፣ የአንድነት ዘመን እንዲሆን እየተመኘሁ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ግዳጅ ላይ የሚገኙ የሠራዊት ዓመራሮችና አባላት፣ ለመላው የምዕራብ ዕዝ አመራር፣ አባላትና ሲቪል ሰራተኞች እንኳን አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ።



ኮሎኔል አማረ ዋኘው የምዕራብ ዕዝ መገናኛና ኢንፎርሜሽን መምሪያ ኃላፊ



ኮሎኔል ዘሪሁን ተረፈ በሰሜን ምዕራብ ዕዝ የክፍለ ጦር አዛዥ

በ2017 ዓ.ም ክፍለ ጦራችን በዋናነት ተልዕኮዋን የተወጣችው በአማራ ክልል ነው። በአካባቢውም አንፃራዊ ሠላም እንዲሰፍን በትጋት፣ በቁርጠኝነት፣ በጀግንነት ተልዕኮዋን በተገቢው ተወጥታለች። በአማራ ክልል መሳሪያ ታጥቀው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ክልሉን የብጥብጥና የትርምስ ቀጣና ለማድረግ ያልተቋረጠ ሙከራ ቢያደርጉም ክፍለ-ጦራችን በተሰማራችበት የግዳጅ ቀጣና ከሌሎች የፀጥታ አካላት ጋር በመመከትና በመደምሰስ ግዳጇን በተገቢው በመወጣት የዘራፊውን ቡድን ህልም አምክናለች። በቀጣይም ክፍለጦራችን ይህን ጥንካሬዋን በማስቀጠል በአዲሱ 2018 ዓ.ም የኢትዮጵያን ሠላም በፅኑ መሠረት ላይ ለመገንባት አመራርና አባሉ ከመቸውም ጊዜ በላይ ቁርጠኛ መሆናቸውን እያነሳሁ ለመላ የክፍለ-ጦራችን አመራርና አባላት እንዲሁም ሲቪል ሰራተኞች ለ2018 ዓ.ም አዲስ ዓመት አንኳን አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ አመሰግናለሁ!!

* * *



ኮሎኔል ገ/ህይወት በለጠ ከማዕከላዊ ዕዝ

እኛ ኢትዮጵያዊያን የራሳችን መገለጫ፤ የማንነታችን ጉልህ ማሳያ የሆኑ በርካታ ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ሀይማኖታዊና መሠል መገለጫዎች ያሉን ህዝቦች ነን። ከእነዚህም አንዱ የአዲስ ዓመት ዘመን መለወጫ ነው። አዲስ ዓመት በአዲስ መንፈስ ለስራ የምንነሳሳበት ወቅት ነው። እኛም እንደ ሠራዊት ባለፈው ዓመት በሀገር ላይ የተደቀኑ ፈተናዎችን በመመከት፤ የህዝብን ሠላምና ደህንነት በማረጋገጥ ረገድ የትኛውም ውጣውረድ ሳይበግረን ፀረ-ሠላም ኃይሎችን በመደምሰስ ዕዛችን ዳሎል በተሰጠው ሰፊ የግዳጅ ቀጠና ሁሉ ህዝቡ የተሻለ የሠላም አየር እንዲተነፍስ ያስቻሉ ድሎችን አስመዝግበናል። አዲሱ ዓመት በሀገራችን ኢትዮጵያ አስተማማኝ ሠላም የሚሰፍንበት የእድገትና የጤና ዘመን እንዲሆን መልካም ምኞቴ ነው። ለቤተሰቦቼ፣ ለማዕከላዊ ዕዝና ለመላው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት እንዲሁም ለኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ እንኳን ለአዲስ ዓመት አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ።

* * *



ኮሰኔል ነጋሽ ኢሬ የሰሜን ምስራቅ ዕዝ ሎጀስቲክስ ኃላፊ

በቅድሚያ ለመላው የዕዙ ዓመራር፣ አባላትና የሰራዊቱ ቤተሰቦች እንዲሁም ኢትዮጵያውያን እንኳን ለ2018 ዓ.ም አዲስ ዓመት አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ። አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የእድገትና የስኬት ዘመን እንዲሆንም እመኛለሁ። የሰሜን ምስራቅ ዕዝ ሎጀስቲክስ ባለፈው ዓመት በቅንጅትና በትብብር በተሰሩ ስራዎች ለተዋጊ ክፍሎች አስተማማኝና ያልተቆራረጠ የውጊያ ድጋፍ አድርጏል። ዕዙ ላስመዘገባቸው ድሎች የሎጀስቲክስ ክፍሉ የላቀ አበርክቶት ነበረው። በአዲሱ 2018 አመትም የክፍሉን ጥንካሬ ለማስቀጠል ቁርጠኝነቱና አቅሙ አለ።



በቅድሚያ ለመላው ኢትዮጵያዊያን፣ ለመከላከያ ሠራዊቱ ከፍተኛ አመራሮች፣ ለሜካናይዝድ አመራርና አባላት እንኳን ለ2018 ዓ/ም አዲስ አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ። አዲሱ ዓመት የነበረንን የስራ ተነሳሽነትና ትጋት የምናስቀጥልበት፣ ታላቅ ድሎችን የምናስመዘግብበት፣ ሀገራችን ሠላም የምታገኝበት እንዲሆን መልካም ምኞቴን መግለፅ እፈልጋለሁ። የተጠናቀቀው 2017 አመት በሁሉም ዘርፍ የላቀ ውጤት ያረጋገጥንበት ሆኖ አልፏል። በቀጣይም ይህን አጠናክረን ለማስቀጠል ዝግጁነታችን አስተማማኝ ነው። ዕዙ የሚሠጠውን ግዳጅ በአነስተኛ ኪሳራ የመፈፀም ብቃትና አቅም አለው።

ኮሎኔል ከማል ገለቶ አገቶ የሜካ/ድ ዕዝ አዛዥ ፅ/ቤት ኃላፊ

* * *



ሌትናል ኮሎኔል ተስፋዬ ደሳለኝ የ24ኛ ጸናት ክፍለ ጦር አዛዥ

24ኛ ጸናት ክፍለ ጦር የደማቅ ታሪክ ባለቤትና የአንደኛ ደረጃ የላቀ የአውደ ውጊያ ጀግና ሜዳይ ተሸላሚ ክ/ጦር እንደመሆኑ በርካታ ስኬታማ ተግባራትን እና ድሎችን ሲያስመዘግብ ቆይቷል። በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ከህወሃት ጋር በተደረጉ ጦርነቶች ከጠላት ጋር ጉሮሮ ለጉሮሮ ተናንቆ የላቀ ድልና ጀብዱ ከመፈፀሙ ባሻገር አሁን ላይ በተሰማራንበት የግዳጅ ቀጣና በከፍተኛ ወኔ አሸባሪው ሸኔን ድባቅ እየመታ ይገኛል። የተለመደውን የጀግንነት ተግባር በመፈፀም ለቀጣናው ህዝብ ሰላም በጥሩ ስኬት መስራትም ችሏል። ክፍለጦሩ የምእራብ ዕዝ 401ኛ ቴዎድሮስ ኮር ስያሜዋን በመስጠት ጭምር መስራች አሃድ እንደመሆኑ ከ53ኛ ናደው እና ከ55ኛ አብዲሳ አጋ ክፍለ-ጦሮች ጋር በተናበበና በተቀናጀ መልኩ አኩሪ ድሎችን እያስመዘገበ ይገኛል። እንደሚታወቀው በጸረ-ሽምቅ እንቅስቃሴ ጠላትን ከገባበት ገብቶ መምታት፣ መደምሰስ፣ መማረክ የክፍለ ጦራችን ባህል ነው። በ2017 ዓ.ም ያሳካናቸውን ድሎች በማስጠበቅ በ2018 አዲስ ዓመትም ለአዲስ ድልና ስኬት እንተጋለን። አዲሱ አመት ለመላው ህዝባችን፣ ለመከላከያ ሠራዊታችን፣ ለክ/ጦራችን አመራርና አባላት በሙሉ የስኬትና የድል አመት እንዲሆን እመኛለሁ።



ሌ/ኮ ከሊፋ ኢታና የ53ኛ ናደው ክፍለጦር አዛዥ

53ኛ ናደው ክፍለ ጦር ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በጀግንነት ታሪክ እየጻፈ የመጣ ክፍለ ጦር ነው። ወደኋላ መለስ ብለን ለማስታወስ ስንሞክር በሰሜኑ ጦርነት በወሎ ግንባር አኩሪ ተጋድሎ መፈፀም ችሏል። በወቅቱም ከኮሩ ተነጥሎ የጠላትን እንቅስቃሴ በመግታትና ጠላትን በመምታት አኩሪ ገድሎችን በመፈፀም ወደ ኮሩ የተመለሰበት ሁኔታ ነበር።

በዳባትና ደባርቅ ዙሪያ በተደረጉ ጦርነቶችም ከፍተኛ ድል ማስመዝገብ የቻለ ክፍለጦር ነው። ከአጎራባች ክፍሎች ጋር በጋራ በመሆንም በበርካታ ቦታዎች በተደረጉ ጦርነቶች ላይ ውጤታማ ስራ እየሰራም መጥቷል።

ከሰሜን ጎንደር ተነስተን ወደ ወለጋ ዞኖች ከገባን በኋላም በተለመደው ጀግንነት የጠላት ኃይልን ትርጉም ባለው መልኩ መምታት ችለናል። በወቅቱ በተሰማራንባቸው ቀጣናዎች አሸባሪው የሸኔ ቡድን ሲፈፅማቸው የነበሩ በርካታ የሽብር ተግባራት ነበሩ። መሰረተ ልማት አልነበረም፣ የመንግስት ተቋማቶች ፈርሰው፤ መንገዶች በሙሉ ዝግ ነበሩ። በመሆኑም ከህዝብ ጋር በመሆን አሸባሪው የሸኔ ቡድንን የገባበት ገብተን በመደምሰስ ውጤታማ ስራ መስራት ችለናል። ባስመዘገብናቸው ድሎች ሳቢያም ፈርሰው የነበሩ መሰረተ ልማቶች እንዲስተካከሉ ምቹ ሁኔታን ፈጥረናል። የመንግስት ተቋማት እንዲደራጁ እና ህብረተሰቡ መደበኛ ስራውን እንዲያከናውን ሆኗል። ክፍለጦራችን በ2017 ዓ/ም ያሳካቸውን ድሎች በ2018 ዓ.ም አጠናክሮ በመቀጠል በቀጣናው የተሟላ ሰላም እንዲሰፍን እንሰራለን። ለክ/ጦራችንና ለተቋማችን የሠራዊት አባላትና አመራር እንዲሁም ለህዝባችን 2018 ዓ.ም ስኬታማ ዓመት እንዲሆንልን መልካም ምኞቴ ነው።

# የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት



ሌ/ኮ ገዛኸኝ በቀለ የ55ኛ አዳሳ ኣጋ ክፍለ-ጦር አዛዥ

ክፍለ-ጦራችን በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ተልዕኮውን ሲፈፅም ቆይቶ ወደ ወለጋ ዞኖች ከገባን ጊዜ ጀምሮ ከሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞን ባሻገርም በተለያዩ ጊዜያት ከቄለም ወለጋ እስከ ምስራቅ ወለጋ የአሸባሪው ሸኔ ቡድንን የመደምሰስ ስራ ተግባራዊ ስናደርግ ቆይተናል። ስኬታማ ግዳጆችን መፈፀም በመቻላችንም አሁን በሚታየው ልክ የአካባቢው ማህበረሰብ የነበረውን የሰላም እጦት ማስተካከል ተችሏል። ይህንን ዘላቂ ለማድረግም ክ/ጦራችን ከሌሎች የኮራችን ክፍለ-ጦሮችና አጋር አካላት ጋር በትብብር እየሰራ ይገኛል። ለውጥ ማምጣት የቻልነውም ሠራዊታችን በከፍተኛ ቁርጠኝነት እና ወኔ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ መሰናክሎችን በማለፍና የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመቋቋም ጭምር ነው።

በ2018 አዲስ አመትም ክፍለጦራችን የጀመራቸውን ስኬታማ ስራዎች በማስቀጠል የተሰጠንን ግዳጅ አንድ በአንድ ለቅመን የተሻለ ስራ እንድንሰራ መልዕክቴን እያስተላለፍኩ ለመላው ህዝባችንና ሠራዊታችን መልካም የስኬት ዓመት እንዲሆን ልባዊ ምኞቴ ነው።

* * *



ሻለቃ ተስፋዬ ጌታሁን ከአየር ኃይል

2017 ዓ.ም እንደ ግልም በርካታ ስኬት የተጎናፀፍኩበት፤ እንደ አመራርም ኃላፊነቴን ለመወጣት ብርቱ ጥረት ያደረግሁበት አመት ነው። ወደ አዲሱ ዓመት ስሸጋገርም የሚሰጠኝን ስራና ግዳጅ በተገቢው ለመወጣት ዝግጁና ቁርጠኛ ነኝ። ለቤተሰቦቼ፣ ለስራ ባልደረቦቼ፣ ለአየር ኃይል ዓመራርና አባላት እንዲሁም ለመላው የሰራዊታችን አባላት እንኳን አደረሳችሁ ለማለት እፈልጋለሁ።"



መቶ አለቃ መንግስቱ መኮንን ከስድስተኛ ዕዝ ጥገና

አዲሱ 2018 ዓመት በ2017 ዓ/ም ያረጋገጥናቸውን አኩሪ ድሎች የበለጠ አጠናክረን ለመቀጠል በተሰለፍንበት ሞያ በቁርጠኝነትና በጀግንነት ተልዕኳችንን በአስተማማኝ የምንዋጣበት ይሆናል። ለስራ ባልደረቦቼ፣ ጓደኞቼ፣ ቤተሰቦቼ በሙሉ እንኳን ለ2018 ዓ/ም አዲሱ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ።

* * *

ባለፈው አመት በተመደብንነት የስራ መስክ ውጤታማ ነበር። እኔ በፋይናንስ ክፍል የክፍያ ባለሞያ ነኝ። በተመደብኩበት ዘርፍም አሠራሩ በሚፈቅደው መሠረት ስራዎችን በተገቢው የሠራንበት አመት ነው። በቀጣይም የዕዙን የፋይናንስ አገልግሎት ለማሳለጥ ባለፈው ዓመት የነበሩን ጥንካሬዎች በማስቀጠል የተሻለ የፋይናንስ ስርዓትና አገልግሎት የምንሰጥበት ይሆናል። ለስራ ባልደረቦቼ፣ ጓደኞቼ፣ ቤተሰቦቼና መላው የመከላከያ አባላት እንኳን ለአዲሱ አመት አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ።

ም/መ/አ ዳኛነሽ ፍቅርአዲስ ከሜካናይዝድ ዕዝ





ውትድርና ፈተናዎችን አሸንፎ የሀገርን ሉዓላዊነትና የህዝብን ሠላም መጠበቅ ነው። እኔም የትልቅ ሀገር ወታደር በመሆኔ ትልቅ ኩራት ይሰማኛል። ባለፈው 2017 ዓ.ም እንደ ወታደር የተሰጠኝን ግዳጅ በቁርጠኝነትና በታማኝነት ተዋጥቻለሁ። በአዲሱ 2018 ዓመትም በተሻለ ዝግጁነት የሚሰጠኝን ግዳጅ ሴትነት ሳይበግረኝ ከጓዶቼ እኩል ማንኛውንም መስዋዕትነት በመክፈል ግዳጄን ለመወጣት ቁርጠኛ ነኝ። ለጓዶቼ፣ ለሁሉም የመከላከያ ሠራዊት አባላትና ለቤተሰቦቼ መልካም አዲስ ዓመት ይሁንላችሁ ለማለት እወዳለሁ።

፲/አ አዳማ መሀመድ ከማዕከላዊ ዕዝ 91 ኛ ክፍለ-ጦር

ያሳለፍነው ዓመት በርካታ ውጤታማ ግዳጆችን የፈፀምንበት ዓመት ነው። በተለይም በአየር ኃይል ደረጃ ሴቶች ተልዕኳቸውን በላቀ ትጋት የፈፀሙበት ጠንክረው በመስራታቸውም በአብራሪነት፣ በጥገና ሞያ፣ በአመራርነት ውጤታማ የሆኑበት ነበር። አዲሱ አመት የተሻለ ስራ የምንሰራበት፣ ሰላም የሚሰፍንበት፣ አንድነት የሚፀናበት ይሆን ዘንድ መልካም ምኞቴን እየገለፅኩ ለአየር ኃይል አመራርና አባላት እንዲሁም ሲቪል ሰራተኞች እንኳን አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ።

፲/አለቃ ውዴ አስካጀኝ ከአየር ኃይል



* * *



በ2017 ዓ/ም በርካታ ግዳጆችን ተወጥተናል። ግዳጅ በመወጣት ሂደት እኔም እንደ ወታደር ተልዕኮየን በትክክል በማወቅ የሚጠበቅብኝን አድርጌያለሁ። ኃላፊነታችንን በመወጣታችንም በተሰማራንባቸው የግዳጅ ቀጣናዎች ሠላም ማረጋገጥ ችለናል። በአዲሱ 2018 ዓመትም በተሻለ በመስራት ሀገሬን ለመጠበቅና ተቋሜ የሚሰጠኝን ግዳጅ ለመወጣት ዝግጁ ነኝ።ለመላዉ የሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት፣ ለጓድኞቼና ቤተሰቦቸ እንኳን ለአዲሱ አመት በሰላም አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ።

፲/አ ሳሊም ረሽድ ከልዩ ዘመቻዎች ዕዝ

በቅድሚያ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ እና በዱር በገደሉ በጀግንነት ግዳጁን እየተወጣ ላለው መላው ሠራዊታችን እንኳን ለ2018 ዓ/ም አደረሳችሁ አደረሰን ማለት እወዳለሁ። 2017 ዓ/ም ግዳጅ በተወጣንባቸው ሰሜንና ምዕራብ ጎጃም ቀጣናዎች ውጤታማ ስራዎችን ማከናወን የቻልንበት አመት ነበር። ለ2018 አዲስ ዓመትም የላቀ ግዳጅ ለመፈፀም ዝግጅት አድርገናል። የጀመርናቸውን ህግ የማስከበር ተግባር አጠናክረን በማስቀጠል ሰላማዊ ከባቢ ለመፍጠር እንተጋለን። በመጨረሻ በጦርነት ስጋት ውስጥ ላለው የትግራይ ህዝብ ዳግም ጦርነት እንዳይገጥመውና እፎይታ እንዲያገኝ ልባዊ ምኞቴ ነው።



ሌተናል ኮሎኔል ነጋ ገ/ማርያም የምስራቅ ዕዝ 791ኛ ሻለቃ አዛዥ



የኢትዮጵያ ባህር ኃይል ትልቅ ክፍል ነው። እየተደራጀ ለሚገኘው የዚህ ታሪካዊ ክፍል አባል በመሆኔ ደስተኛ ነኝ። ክፍሉ በቀደሙት ዘመናት ገናና ስም እንደነበረው የታሪክ ድርሳናት ይናገራሉ። እንደገና የተደራጀው የኢትዮጵያ ባህር ኃይል ከዚህ በፊት ከነበረው ዝና እና ታሪክ ከፍ ያለ እንዲሆን የበኩሌን አስተዋፅዖ ለመወጣት ዝግጁ ነኝ። የፈረሰውን ባህር ኃይል የመለሰው ትውልድ አካል በመሆኔም ደስተኛ ነኝ። ለባህር ኃይል አመራርና አባላት፣ ለሲቪል ሰራተኞችና ለቤተሰቦቼ እንኳን ለ2018 ዓ/ም አዲስ አመት በሰላም አደረሳችሁ እላለሁ።

ኮማንደር የሸዋስ ጥላሁን ከኢትዮጵያ ባህር ኃይል

በተሰማራንበት የግዳጅ ቀጣና የተሰጠንን ተልዕኮ በአግባቡ በመወጣት የህዝብና የሀገር አደራን እየፈፀምን እንገኛለን። በ2017 ዓ/ም ስኬታማ ስራዎችን ማከናዋን ችለናል። በተልዕኳችን ህዝባዊ ወገንተኝነታችንን ጠብቀን ለጋራ ግብ እየሰራን ነው። መጪው 2018 አዲስ ዓመት ለመላው ህዝባችንና ሠራዊታችን የስኬት ዓመት እንዲሆንልን እየተመኘሁ መልካም አዲስ ዓመት እላለሁ።

ም/መ/አ ራሒማ ቱሳ ከምስራቅ ዕዝ 301ኛ ኮር



* * *

ያለፈው ዓመት የተሰጠንን ግዳጅ በተገቢው የተዋጣንበትና ውጤት ያስመዘገብንበት ነው. በዕዙ የግዳጅ ቀጣና የሚንቀሳቀሱ ፀረ-ሰላም ኃይሎችን ተከታትሎ በመደምሰሱ ሒደት የበኩሌን አስተዋፅዖ አድርጌያለሁ። ቀጣይም የሚሰጠኝን ግዳጅ በተገቢው ለመወጣት ዝግጁ ነኝ። ለመላ የዕዛችን የሠራዊት አባላት፣ ጓደኞቼና ቤተሰቦቼ እንኳን ለአዲሱ 2018 ዓ.ም እንኳን አደረሳችሁ ማለት እወዳለሁ።

ም/መ /አለቃ ፍቃዱ ይግዛው ከደቡብ ዕዝ



* * *




ያለፈዉን ዓመት ከስራ ባልደረቦቼ ጋር በጋራ በመሆን የተሰጠኝን ግዳጅ በጥሩ ሁኔታ ተዋጥቻለሁ። ዉትድርና የቡድን ስራ ቢሆንም ስራዉ ዉጤታማ የሚሆነው ግለሰቦች ኃላፊነታቸውን በትክክል ሲዋጡ ነው። እኔም በዚህ አግባብ በ2017 ዓ/ም የተሰጠኝን ስራ በአግባቡ በሚገባ ተዋጥቻለሁ። በቀጣይ 2018 ዓ/ም የሚሰጠኝን ግዳጅ ውጤታማ በማድረግ የተቋሙን ተልዕኮና ራዕይ ከግብ ለማድረስ የድርሻየን ለመወጣት ዝግጁ ነኝ። ለልዩ ዘመቻዎች ዕዝ የሰራዊት አባላት፣ ጓድኛቼ፣ ቤተሰቦቼ እንኳን ለአዲሱ አመት አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ።

ም/፲/አለቃ አለምነዉ ደስታ ከልዩ ዘመቻዎች ዕዝ

ለ6ኛ ዕዝ አመራርና አባለት እንዲሁም ሲቪል ሰራተኞች እንኳን ለ2018 ዓዲስ አመት አደረሳችሁ እያልኩ መከላከያ ሠራዊት ለህዝብ ሠላምና ደህንነት ሲል ውድ ህይወቱን ሳይሰስት የሚሰጥ የምንጊዜም ጋሻና መከታ ነው። እኛ የተቋሙ ሲቪል ሠራተኞችም ከመከላከያ ጎን ሆነን ለምንሰጠው አገልግሎት ደስተኞች ነን። ቀጣይም ከሠራዊታችን ጎን በመሆን የምንሰጠውን አገልግሎት አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል።

ወ/ሮ ገነት አበበ የ6ኛ ዕዝ ሲቪል ሰራተኛ




















## በዓመቱ የሠራዊታችን የሥራ አፈፃፀም በፎቶ ሲቃኝ















**የመከላከያ ሠራዊቱን ማዘመን የኢትዮጵያን ሠላም አስተማማኝ ያደርጋል!**